ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ዓርብ

82ኛ ዓመት ቁጥር 188 መጋቢት 8 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



# በመንግሥትና በግል አጋርነት 100 ሺህ ቤቶች ሊገነቡ ነው

## - 68 አልሚዎች የ 30/70 የቤት ግንባታ ለማከናወን ውል ፈጸሙ

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በመንግሥትና በግል አጋርነት በመጀመሪያ ዙር የ 100ሺህ ቤቶች ግንባታ እንደሚከናወን አስታወቀ። በመንግሥትና በግል አጋርነት የሚገነቡ የ 30/70 የማህበር ቤቶችን ለመገንባት 68 የሀገር ውስጥና የውጭ አልሚ ድርጅቶች ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጋር ትናንት የውል ስምምነት ፈጽመዋል።

በፊርማ ሥነ ሥርዓቱ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ እንደገለጹት፤ መንግሥት የዜጎችን የመኖሪያ ቤት እጥረት ለመቅረፍ የሚረዳ በመንግሥትና በግል አጋርነት የ 30/70 ማህበር ቤቶችን በሁለት ዓመት ያስገነባል።

በሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት ውስጥ የ 100 ሺህ ቤቶች ግንባታ ተጠናቆ መካከለኛ ገቢ ላላቸው የከተማዋ ዜጎች በአነስተኛ ወጪ ተደራሽ ይደረጋል ብለዋል።

ለቤቶቹ ግንባታ 350 ሄክታር መሬት በተለያዩ ክፍለ ከተሞች መዘጋጀቱን አስታውቀው፤ በስምምነቱ መሰረት አልሚዎች በመጀመሪያ ዙር በሁለት ሳምንታት ውስጥ የመስሪያ ቦታ እንደሚረከቡ አስታውቀዋል።

በመንግሥትና በግል... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ዶክተር ዮናስ አዳዬ

## “በአገራዊ ምክክሩ ሒደት የውጭ ጣልቃ ገብነት አይኖርም”

ገጽ 4

# በአዲስ አበባ በቂ ምርት እንዲኖር እየተሰራ ነው

## - ነጋዴዎችና የኅብረት ስራ ማኅበራት ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋና በስፋት ማስገባት ጀምረዋል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ የተከሰተውን የኑሮ ውድነት ለማረጋጋት የኦሮሚያ ነጋዴዎችና የኅብረት ስራ ማህበራት ለአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ የጤፍ፣ የስንዴና የበቆሎ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋና በስፋት ማቅረብ ጀመሩ።

የኦሮሚያ ክልል ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አወሉ አብዲ እንደተናገሩት፤ የኦሮሚያ ክልል በአዲስ አበባ ከተማ በቂ ምርት እንዲኖር እና ኅብረተሰቡ በተመጣጣኝ ዋጋ የግብርና ምርቶችን እንዲያገኝ ከአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ጋር በጋራ እየሰራ ነው።

በከተማዋ በተለያዩ ቦታዎች በኦሮሚያ ህብረት ስራ

በአዲስ አበባ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ፡ ኢዮብ ተፈሪ















# በአፋር ክልል የጎርፍ አደጋን ለመከላከል የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥራ በመሠራት ላይ ነው

**ማርቆስ በላይ**



አዲስ አበባ፡- በአፋር ክልል በተደጋጋሚ የሚከሰተውን የጎርፍ አደጋን ለመከላከል የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥራ በመሠራት ላይ መሆኑን የአፋር ክልል የቅድመ ማስጠንቀቂያ እና ምላሽ ቢሮ አስታወቀ።

የቢሮው የቅድመ ማስጠንቀቂያ እና ምላሽ ዳይሬክተር አቶ ማሂ አሊ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥራው የጎርፍ አደጋ ሥጋት አለባቸው ተብለው በተለዩ ቦታዎች በመሰራት ላይ ነው። በተለይም የአዋሽ ወንዝ ተፋሰስ ሥር ያሉ ጠቅላላ ወረዳዎች ላይ የጎርፍ ቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥራዎች ለሕዝቡ እየተሰጡ ነው።

እንደ አቶ ማሂ ገለጻ፤ የአደጋው ሥጋት ባለባቸው የክልሉ አካባቢዎች ላይ ኅብረተሰቡን ባሳተፈ መልኩ የጎርፍ መሄጃ መስመሮችን ለማጠናከር በመሠራት ላይ ሲሆን አርሶ አደሮች በወቅቱ ያላቸውን የደረሱ የእርሻ ላይ ምርቶችን እንዲሰበስቡ የግንዛቤ ሥራ በመሰራት ላይ ነው። በተለይም የአካባቢው ነዋሪዎች አርብቶ አደሮች በመሆናቸው ያሏቸውን እንስሳት እና መኖ በመሰብሰብ የአደጋው ሥጋት ካለባቸው ቦታዎች ወደ ተሻለ ቦታዎች እንዲወስዱ የሚያስችል ቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥራ በመሠራት ላይ ነው።

በክልሉ አደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ደረጃ የጎርፍ አደጋ መከላከል ግብረ ኃይል መቋቋሙን የገለጹት ዳይሬክተሩ፤ የጎርፍ አደጋው ከመከሰቱ በፊት ግብረ ኃይሉ አፋጣኝ የምላሽ ሥራ በጊዜ እንዲሰጥ ለማድረግ የሚያስችል ሲሆን ዜጎች ጉዳትም ሆነ የመፈናቀል አደጋ ቢደርስባቸው ምላሽ ለመስጠት በሚያስችል መልኩ የተቋቋመ ነው። ግብረ ኃይሉ ከእያንዳንዱ የክልል ቢሮዎች፣ የውጭ ድርጅቶችንና ኤጀንሲዎች ባሳተፈ መልኩ የተቋቋመ ሲሆን በአደጋ ሥጋት አመራር ኮሚሽን በኩል የሚመራ መሆኑን ገልጸዋል።

በክልሉ ዝናብ እየዘነበ መሆኑን የገለጹት አቶ ማሂ፤ የአደጋው ሥጋት አለባቸው ተብለው በተለዩት አካባቢዎች ላይ እስካሁን የደረሰ አደጋ አለመኖሩን ጠቅሰው አዋሽ ተፋሰስ ዙሪያ በሚገኙ በገቢረሱ ዞን አሚባራ፣ አዋሽ ፈንታሌ፣ ጉለቻ፣ ገዋኔ፣ ገላሉ እና ሀሩካ የሚባሉ አካባቢዎች በአብዛኛው የጎርፍ አደጋ ሥጋት ያለባቸው መሆናቸውን አስረድተዋል።

በተለይም የታችኛው አዋሽ ሚሌ፣ ቡኪ፣ አሳይታ፣ አፋምቦ፣ ገረኒ አካባቢዎች ላይ በከፍተኛ ሁኔታ ለጎርፍ አደጋ ተጋላጭ ይሆናሉ ተብለው የተለዩ መሆናቸውን በመጥቀስ፤ እነዚህም ለአዋሽ ወንዝ ቅርበት ያላቸው አካባቢዎች መሆናቸውን እና በግብረ ኃይሉ በኩል ፈጣን ምላሽ ለመስጠት ዕቅድ የሚዘጋጅ መሆኑን ኃላፊው ገልጸዋል።

በአፋር ክልል በዓመቱ በዝናብ ወቅት በአዋሽ ወንዝ መሙላትና ደራሽ ጎርፍ በሚያስከትለው የጎርፍ መጥለቅለቅ ሳቢያ በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ላይ ተደጋጋሚ ጉዳት ይደርሳል።

# የአዕምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች በኢኮኖሚው ተጠቃሚ እና ተሳታፊ እንዲሆኑ መስራት ያስፈልጋል

**ማህሌት ብዙነህ**




አዲስ አበባ፡- የአዕምሮ ዕድገት ውስንነት ያለባቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች በኢኮኖሚውና በማህበራዊ መስክ እኩል ተጠቃሚ እና ተሳታፊ እንዲሆኑ መስራት እንደሚገባ የፍቅር የኢትዮጵያ የአዕምሮ ውስንነት ብሔራዊ ማህበር አስታወቀ። የአዕምሮ ዕድገት ውስንነት ያለባቸው "የዳውንሲንድረም" ቀን በዓለም አቀፍ እና በኢትዮጵያ ደረጃ መጋቢት 10 ቀን እንደሚከበር ተጠቁሟል።

የፍቅር የኢትዮጵያ የአዕምሮ ውስንነት ብሔራዊ ማህበር ፣ ከኢፌዴሪ ሴቶች እና ህጻናት ሚኒስቴር እና ሌሎች አጋር አካላት በጋራ በመሆን ‹ከእኛ ጋር ስለእኛ እንስራ› በሚል መሪ ቃል በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ12ኛ ጊዜ በኢትዮጵያ ደግሞ ለ 8ኛ ጊዜ እንደሚከበር በትናንትናው እለት በሰጡት የጋራ መግለጫ አስታውቀዋል።

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሴቶች እና ህጻናት ሚኒስቴር የአካል ጉዳተኞች ጉዳይ መሪ ስራ አስፈጻሚ አቶ አሰለፈው አህመዲን በወቅቱ እንደገለጹት፣ የአዕምሮ ዕድገት ውስንነት ያለባቸው ልጆች በሁሉም መስኮች አካታችነት ከተረጋገጠ እንደማንኛውም የማኅበረሰብ ክፍል መማር፣ መስራት ፣ ቤተሰብ መመስረት እንደሚችሉ ያላቸውን እምቅ አቅም ማሳየት አለባቸው።

የአዕምሮ ዕድገት ውስንነት ያለባቸው እና የአካል ጉዳተኞች መብቶቻቸው ሊጠበቁላቸው የሚገባው ስለሚታዘንላቸው ሳይሆን በሕገመንግሥቱ መብታቸው ስለተረጋገጠ ነው ያሉት አቶ አሰለፈው፤ በጤና ፣ ትምህርት፣ ፍትህና የስራ ዕድል መስኮች ላይ እኩል ተሳትፎ እንዲኖራቸውና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚ እንዲሆኑ መስራት ከመንግሥት ጀምሮ በየደረጃው ያሉ የማኅበረሰብ ክፍሎች ኃላፊነት መሆኑን ገልጸዋል።

የፍቅር የኢትዮጵያ የአዕምሮ ውስንነት ብሔራዊ ማህበር ፕሬዚዳንት ወይዘሮ ምህረት ዘውዴ እንደገለጹት፤ የዓለም አቀፍ የዳውንሲንድረም ቀን የአዕምሮ ዕድገት ውስንነት ያለባቸው ወገኖች፣ ከቤተሰቦቻቸው እና አጋር አካላት ጋር በጋራ በመሆን በማናቸውም መስኮች የመካተት እና ስለደህነታቸው መጠበቅ በአንድ ድምጽ በማሰማት ይከበራል። ይህ በዓል ለህብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ከመስራት ባለፈ የአዕምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸውን ከተደበቁበት ወጥተው ወደ ኅብረተሰቡ እንዲቀላቀሉ ለማድረግ ፣ የሚደርስባቸውን አድሎ እና መገለል ለማስቀረት ፣ እኩል ተጠቃሚ እና ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ ዓላማ ይዞ የሚከበር መሆኑን ወይዘሮ ምህረት ገልጸዋል።

በባዓሉ ዕለት ከኢትዮ - ኩባ የወዳጅነት ፓርክ ወደ መስቀል አደባባይ የእግር ጉዞ የሚደረግ ሲሆን አንድ ሰው ከአንድ የአዕምሮ እድገት ውስንነት ተጠቂ ጋር እጅ ለእጅ እንዲያያዙ በማድረግም በኅብረተሰቡ ዘንድ ያለውን የመገለል እና የመሸማቀቅ ባህሪ ለማስቀረት ይሰራል ተብሏል።

በዓለም ጤና ድርጅት አሃዛዊ መረጃ መሰረት ከዓለም ሕዝብ ውስጥ በአማካኝ 3 በመቶ የሚሆኑት የአዕምሮ ዕድገት ውስንነት እንዳለባቸው ይነገራል። በዚህ ስሌት መሰረት በኢትዮጵያ ውስጥ ከ5 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ የአዕምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች እንዳሉ ይገመታል። በሀገራችን ውስጥ ያሉት የአዕምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ከፍተኛ አድሎ እና መገለል ይደርስባቸዋል። በተጨማሪም የአዕምሮ ውስንነት ያለበት ልጅ መውለድ የሚያሸማቅቅ እና እንደ እርግማን የሚታይበት ሁኔታ መኖሩን መረጃዎች ይጠቁማሉ።

ይህ ማኅበርም ተደራሽነቱን በማስፋት በማኅበረሰቡ ዘንድ ያለውን አስተሳሰብ ከመለወጥ ባለፈ የአዕምሮ ዕድገት ተጠቂዎች ምቹ የኑሮ ሁኔታዎችን ለመፍጠር እንደሚሰራ የገለጹት ወይዘሮ ምህረት ፤ በዚህ ቀንም ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ተሳታፊ እንዲሆን ወይዘሮ ምህረት ጥሪ አቅርበዋል።



አቶ ኡስማን ሱሩር

# ክልሉ በበልግ ወቅት አንድ ሚሊዮን ሄክታር ያህል መሬት በሰብል ለመሸፈን እየሠራ ነው

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- በደቡብ ክልል በበልግ ወቅት አንድ ሚሊዮን ሄክታር ያህል መሬት በሰብል ለመሸፈን እየሠራ መሆኑን የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታወቀ።

የደቡብ ክልል ግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ኡስማን ሱሩር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ የበልግ ዝናብ የዘገየ ቢሆንም የማሳ ዝግጅት በሁሉም የበልግ አምራች አካባቢዎች ተጀምሯል። በዚህም በአንድ ሚሊዮን ሄክታር ያህል መሬት ዓመታዊ እና ቋሚ ሰብሎች ለማልማት ዕቅድ ተይዞ እየተሠራ ነው።

ከዚህ ውስጥም ከ900 ሺህ ሄክታር መሬት በላይ የሚሆነው በዓመታዊ ሰብሎች፣ 33 ሺህ ሄክታር መሬት ደግሞ በፍራፍሬ እና 41 ሄክታር መሬት በእንሰት ሰብል በመሸፈን ከ102 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ይገኛል ተብሎ ይታሰባል ብለዋል ቢሮ ኃላፊው።

በሀገራችን የተከሰተው ድርቅ በክልላችንም በአንድ አንድ አካባቢዎች ላይ አጋጥሟል ያሉት አቶ ኡስማን፤ በደቡብ ኦሞ እና ኮንሶ ዞኖች ላይ ከባድ የሚባል ጉዳት ማድረሱን ለአብነት አንስተው አስረድተዋል። ድርቁም ወደ ርሃብ እንዳይቀየር ክልሉ በንቅናቄ ብዙ ስራዎችን እየሰራ ባለበት ወቅት ይህ የበልግ ዝናብ መዝነቡ ለክልሉ እፎይታ የሚሰጥ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

እንደ ኃላፊው ገለፃ፤ በዚህ ወቅት የበልግ ዝናብ መዝነቡ ትልቅ ፋይዳ አለው። ለእንስሳት ውሃ በቀላሉ ለማቅረብ ዕድል ከመስጠቱም ባሻገር ለእንስሳት መኖ በቀላሉ ለማግኘት ያስችላል። በተጨማሪም ድርቅ ባለባቸው አካባቢዎች ፈጥነው የሚደርሱ የሰብል አይነቶችን አርሶ አደሮች ተገቢውን ዝግጅት አድርገው ማልማት እንዲችሉ ዕድል ይፈጥራል።

እያንዳንዱ አካባቢ የሚገኝን እርጥበት ማሳ ውስጥ የማስቀረት ስራም ትኩረት ተሰጥቶ እንዲሰራ ያስቀመጥነው አቅጣጫ አለ ያሉት ኃላፊው፤ ይህም በየደረጃው በባለሙያ እንዲደገፍ የማድረግ እና ለውጤት እንዲደርስ የጋራ ርብርብ ያስፈልጋል ብለዋል።

እቅዱንም ውጤታማ ለማድረግ በክልልም በዞንም ደረጃ ያሉ አመራሮች በተገኙበት የጋራ ንቅናቄ መድረክ በዚህ ሳምንት ይኖረናል ያሉት አቶ ኡስማን፤ ከንቅናቄው በተጨማሪም የበልጉ ዝናብ መዝነቡ ያስቀመጥነውን ግብ ለማሳካት እና አጠቃላይ እርሻ ዝግጅቱን ለማጠናከር ትልቅ ሚና ይጫወታል ብለዋል።



አቶ ጌቱ ገመቹ

## በኦሮሚያ ክልል የተሰራው የተፋሰስ ልማት ስራ በምርትና ምርታማነት ላይ ተጨባጭ ውጤት እያሳየ ነው

### - ለ60 ቀናት ታቅዶ እየተከናወነ ያለው የተፋሰስ ልማት 85 በመቶ ተከናውኗል

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- በክልሉ የተሰራው የተፋሰስ ልማት ስራ በምርትና ምርታማነት ላይ ተጨባጭ ውጤት እያሳየ መሆኑን የኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ አስታወቀ። በክልሉ በ60 ቀናት ውስጥ ለማልማት ከታቀደው 1 ሚሊዮን ሄክታር 85 በመቶ የሚሆነው መከናወኑ ተገለጸ።

የኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ጌቱ ገመቹ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹ፤ የተፋሰስ ልማት ስራው እንደ ክልል ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ ነው። በክልሉ በጥር ወር በ60 ቀናት ውስጥ በዘመቻ የተጀመረው የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ስራ በትኩረት እየተከናወነ መሆኑን የገለጹት ቢሮ ኃላፊው፤ አንዳንድ ዞኖች ከታቀደው የ60 ቀናት የስራ ጊዜ ቀድመው መስራት ጀምረዋል። ከፍተኛ ቁጥር ያለው ማኅበረሰብ በተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ስራው እየተሳተፈ መሆኑን ተናግረዋል።

የልማት ስራው በኅብረተሰቡ ተሳትፎና በዜግነት አገልግሎት እየተከናወነ መሆኑን የገለጹት አቶ ጌቱ፤ የልማት ስራው የአፈር መሸርሸር፣ የተፈጥሮ ሀብትን ወደ ቦታው ለመመለስ እንዲሁም የአየር ንብረት ለውጥን ለመቆጣጠር እየረዳ ነው ብለዋል።

በክልሉ በ60 ቀናት ውስጥ አንድ ሚሊዮን ሄክታር የሚሆን መሬት በተፋሰስ ለማልማት ታቅዶ ወደ ስራ መገባቱን የገለጹት አቶ ጌቱ፤ እርከኖች፣ የውሃ ማቆር ሥራና ሌሎች የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ስራዎች እየተሰሩ ነው። ሁለቱም የሀረርጌ ዞኖች ከዚህ በፊት ከፍተኛ የሆነ የአፈር መሸርሸር የደረሰባቸው ዞኖች ነበሩ። የአፈር መሸርሸርን ለመቀነስ ከፍተኛ ሥራዎችን በማከናወን ለሁሉም የክልሉ አካባቢዎች ብቻ ሳይሆን እንደ አገር ተሞክሮ የሚሆን ስራ መሰራቱን ጠቅሰዋል።

ከታቀደው የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ስራ 85 በመቶ የሚሆነው መጠናቀቁን የገለጹት ኃላፊው፤ ቀሪው 15 በመቶ ባሉት ውስን ቀናት ይጠናቀቃል። ሥራውን ለማከናወን በየደረጃው ያሉ የግብርና አመራሮች 60 ቀን ሙሉ ስምሪት ወስደው እየሰሩ ስለመሆናቸው አንስተዋል።

በኦሮሚያ ክልል እየተከናወነ ያለው የተፋሰስ ልማትና የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ስራ በምርትና ምርታማነት ላይ ምን ያህል ተጨባጭ ለውጥ እያመጣ እንደሆነ አርሶ አደሩ በሚገባ ተገንዝቧል። ከዚህ በፊት በክልል የተሰራው የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራ አንዳንድ ቦታዎች ላይ የጠፉ ኃይቆች ጭምር እንዲመለሱ አስችሏል።

እንደ አቶ ጌቱ ገለጻ፤ በዘንድሮው ዓመት ከ6 ሺ በላይ ተፋሰሶች ወደ ስራ ገብተዋል። በተፈጥሮ ሀብት ጥበቃው አርሶአደሩና አርብቶ አደሩ የተሳተፉበት ስራ መከናወኑን የተናገሩት አቶ ጉቱ፤ ከአስር ሚሊዮን በላይ የሰው ኃይል በተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ስራው ተሳትፎ እያደረገ ነው ብለዋል።

## ለውጭ ገበያ አቅም የሚፈጥሩ የተሻሻሉ የስንዴ ዝርያዎች ለብሔራዊ የዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ ቀርበዋል

### - ዝርያዎቹ በሄክታር 60 ኩንታል ምርት ያስገኛሉ

**ሞገስ ተስፋ**



አዲስ አበባ፡- ስንዴን ለውጭ ገበያ ለማቅረብ አቅም የሚፈጥሩ የተሻሻሉ የስንዴ ዝርያዎች ለብሔራዊ የዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ ማቅረቡን የአማራ ክልል የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት አስታወቀ። ዝርያዎቹ በሄክታር 60 ኩንታል ምርት እንደሚያስገኙም ተገልጿል።

የአማራ ክልል ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ጥላዬ ተክለወልድ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ምርትና ምርታማነትን ሊያሳድጉ የሚችሉ የአገር ውስጥና አገር ውጭ ያሉ ቴክኖሎጂዎችን በማፍለቅ የአርሶ አደሩ ምርታማነት እንዲያድግ ሰፊ ስራ ተሰርቷል። የተለያዩ የምርምር ሂደቶችን አልፈው በሰብል፣ በአትክልትና ፍራፍሬ፤ በእንስሳት ዝርያ ምርታማነትን ከነበረበት ዝቅተኛ ደረጃ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ለማሸጋገር ቴክኖሎጂ ማፍለቅ ላይ በሰፊው እየተሰራም ነው።

የፈለቁ ቴክኖሎጂዎችን ለዘር አብዥዎች በማቅረብ ለአርሶ አደሩ እንዲደርሱ እየተሰራ መሆኑን የገለጹት ዋና ዳሬክተሩ፤ ከዚህ በፊት በምርምር ውጤታማ የሆኑ እንደ ገብስ፣ ስንዴ፣ በቆሎና ሌሎች የሰብል ዝርያዎች ለአርሶ አደሩ ቀርበው ምርታማነቱን እንዲያሳድግ አድርገዋል። የሚፈልቁ ቴክኖሎጂዎች አርሶ አደሩ ግንዛቤ እንዲኖረው በማድረግ የሰርቶ ማሳያ የመስራት ተግባር እንደሚከናወን ተናግረዋል።

እንደ ዶክተር ጥላዬ ገለጻ፤ ኢንስቲትዩቱ የአርሶ አደሩን ምርታማነት የሚያሳድጉ በሽታዎችን የሚቋቋሙ የሰብል ዝርያዎችን ለዘር አብዥዎች በማቅረብ ለአርሶ አደሩ የሚሰራጩበት ዕድል እተየፈጠረ ነው። በአማራ ክልል ከ1 ነጥብ 4 ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት አሲዳማ አፈር ሲሆን ይሄም ለማምረት ትልቅ ችግር ነው። በዚህም የተነሳ አርሶ አደሮች መሬታቸው ላይ ምርት ማምረት እንዳይችሉ አድርጓል።

አርሶ አደሮች መሬታቸው በአሲዳማ አፈር ሲጠቃ ማምረት የማይችሉበት ደረጃ ይደርሳሉ። በዚህ የተነሳ በመቶ ሺዎች የሚቆጠር ሄክታር መሬት ከምርት ውጭ ይሆናል። እነዚህ አዳዲስ ስንዴ ዝርያዎች ችግሩን ከመቅረፍ አኳያ አሲዳማ አፈር ባለባቸው አካባቢዎች ላይ ስንዴን በውጤታማነት ለማምረት የሚያስችሉ መሆናቸውን ዶክተር ጥላዬ ገልጸዋል።

በዚህ አመት ማሪጋና ቲናሙ 11 የተሰኙ የስንዴ ዝርያዎች ለብሔራዊ የዝርያ አጽዳቂ ቀርበዋል። ዝርያዎቹ አሲዳማ አፈርን በመቋቋም ምርታማነትን ማሳደግ የሚችሉ ዝርያዎች ናቸው። የተገኙት የስንዴ ዝርያዎች ውጤት እንዲሁ በቀላሉ የተገኘ የምርምር ውጤት ሳይሆን ሰፊ ጊዜና በጀት ወስደው የተገኙ ናቸው። ዝርያዎቹን እንደ አገር በሚገባ መጠቀም ከተቻለ የስንዴ ምርታማነትን በማሳደግ ኢትዮጵያ ለያዘችው ስንዴን ለውጭ ገበያ የማቅረብ ስራ ስኬታማነት አዎንታዊ አቅም የሚሆን ነው።

ለብሔራዊ አጽዳቂ ኮሚቴ የቀረቡት ዝርያዎች በሚቀጥለው ዓመት በስፋት ለአርሶ አደሩ እንዲሰራጩ ይደረጋል። እንደ ሀገር የተያዘውን የስንዴ ምርትን የማሳደግ ዕቅድ በማሳደግ ቀጥተኛ አስተዋጽኦ የሚሰጡ ናቸው። በበጋ መስኖ በቂ ስንዴ ማምረት የሚቻልበትን እድል ሊፈጥሩ የሚችሉም ናቸው።

በየዘርፉ በርካታ ቴክኖሎጂዎች አሉ ያሉት ዶክተር ጥላዬ፤ የተሻሻሉ የሰብል ዝርዎች በሄክታር የሚሰጡት ምርት እንደየሰብሉ ዓይነት ይለያያል። ለምሳሌ ጤፍ 25 ኩንታል በሄክታር የሚሰጡ ዝርያዎች አሉ። አዳዲሶቹ የስንዴ ዝርያዎች 60 ኩንታል በሄክታር ይሰጣሉ። በበጋ መስኖ ደግሞ ከዚህም የበለጠ ምርት የሚሰጡበት እድል እንዳለ ገልጸዋል።

## ዲጂታል ሚዲያዎች የጋዜጠኝነት ሙያዊ ሥነ ምግባርን ተከትለው መስራት ይጠበቅባቸዋል

**ጌትነት ምህረቴ**

አዲስ አበባ፡- ዲጂታል ሚዲያዎች የግል ጥቅማቸውን ብቻ ሳይሆን የሀገርንና የሕዝብን ሰላም መሰረት ባደረገ መልኩ የጋዜጠኝነትን ሙያዊ ሥነ ምግባር አክብረው መስራት እንደሚጠበቅባቸው የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ምክር ቤት ገለጸ። የሀሰት መረጃዎችን፣ ግጭት ቀስቃሽና የጥላቻ መልዕክቶችን ከማስተላለፍ መቆጠብ እንዳለባቸውም ተጠቁሟል።

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ምክር ቤት ሰብሳቢ አቶ አማረ አረጋዊ ምክር ቤቱ ትናንት ባዘጋጀው የበይነ መረብ ሥነ ምግባር ደንብ ሥልጠና መክፈቻ ላይ እንደተናገሩት፤ በአሁኑ ጊዜ በዲጅታል ሚዲያው በሚሰራጩ የሀሰት መረጃዎች ፣ የጥላቻ እና ብሄርና ሃይማኖት ተኮር ግጭት ቀስቃሽ መልዕክቶችን የማስተላለፍ ሁኔታ እየጨመረ መጥቷል። ዲጂታል ሚዲያው ሥነ ምግባርን በተከተለ መልኩ መስራት ካልቻለ በሀገር ደህንነትና በሕዝብ ሰላም ላይ ስጋት ስለሚፈጥር የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ምክር ቤትም ዲጂታል ሚዲያዎች የጋዜጠኝነትን ሙያዊ ሥነ ምግባር አክብረው እንዲሰሩ የበይነ መረብ የሥነ ምግባር ደንብ አዘጋጅቷል።

ሀገራዊ ሰላምና ደህንነትን እንዲጠበቅ መስራት የሁሉም ሚዲያ ኃላፊነት መሆኑን አመልክተው፤ ዲጂታል ሚዲያው የሀገርንና የሕዝብን ደህንነትና ሰላም ታሳቢ ባደረገ መልኩ የጋዜጠኝነትን ሙያዊ ሥነ ምግባር በተከተለ መልኩ መስራት እንደሚኖርበት አመልክተዋል።

በአሁኑ ጊዜ የዲጂታል ሚዲያ ተደራሽነት እየጨመረ ነው ያሉት አቶ አማረ፤ ዲጂታል ሚዲያዎች የግል ጥቅማቸውን ብቻ ሳይሆን የሕዝብን ሰላም መሰረት ባደረገ መልኩ የጋዜጠኝነትን ሙያዊ ሥነ ምግባር አክብረው እንዲሰሩ የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ምክር ቤት ባዘጋጀው የበይነ መረብ የጋዜጠኝነት ሥነ ምግባር ደንብ ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨባጫ ሥልጠና መስጠቱን ተናግረዋል።

የጋዜጠኝነትን ሥነ ምግባር የተከተለ ዲጂታል ሚዲያ በሀገር ግንባታና ለሕዝቡ መረጃ ተደራሽ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ሚና እንዳለው ገልጸው፤ በአንጻሩ ሥነ ምግባርን ያልተከተለ፣ ግጭት ቀስቃሽ፤ የሀሰት መረጃዎችንና የጥላቻ መልዕክቶችን የሚያስተላለፉ ዲጂታል ሚዲያዎች የሕዝብ ሰላምና የሀገር ስጋት መሆናቸውን አመልክተዋል።

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን ምክትል ዳይሬክተር አቶ ግዛው ተስፋዬ በበኩላቸው ባለሥልጣኑ በዲጂታል ሚዲያዎች የሚንቀሳቀሱ የመገናኛ ብዙሃን ተቋማት እውቅና የሚያገኙበት አሰራር መዘርጋቱንም ጠቁመው፤ ዲጂታል ሚዲያዎች ለህብረተሰቡ ትክክለኛ መረጃ በማድረስ ረገድ ሙያዊ ሥነ ምግባርን በተከተለ መልኩ መስራት አለባቸው ብለዋል። የዲጂታል ሚዲያዎች ግጭት ቀስቃሽና የጥላቻ መልዕክት ከማስተላለፍ ድርጊታቸው ተቆጥበው ሥነ ምግባርን አክብረው እንዲሰሩ ጠይቀዋል።

በበይነ መረብ ጋዜጠኝነት የሥነ ምግባር ደንብ ላይ ጽሁፍ ያቀረቡት የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ምክር ቤት ምክትል ስራ አስፈጻሚ አቶ ታምራት ሃይሉ በአብዛኛው በዲጂታል ሚዲያው እየተሳተፈ ያለው ከጋዜጠኝነት ሙያ ውጪ መሆኑን ጠቁመው፤ የበይነ መረብ የጋዜጠኝነት ሥነ ምግባር ደንቡ የሚመለከተው በጋዜጠኝነት ሙያ ውስጥ ሆነው በዲጂታል ሚዲያ ተሳትፎ ያላቸውን ነው ብለዋል። በዲጂታል ሚዲያ የሀሰት መረጃ፣ የጥላቻና የግጭት ጉሰማ መልዕክት የሚያስተላልፉት በሙያው ዕውቀቱና ሥነ ምግባሩ የሌላቸው ግለሰቦች መሆናቸውን ለህብረተሰቡ ማሳወቅና ማስገንዘብ እንደሚገባ አስረድተዋል።

ዛሬ ግለሰቦች በዲጂታል ሚዲያዎች የታዋቂ ሰዎችና የፖለቲከኞችን ስም በመጠቀም የሀሰት መረጃና የጥላቻ መልዕክቶች ያስተላልፋሉ ያሉት አቶ ታምራት፤ ስለ ዲጂታል ሚዲያዎች በትክክል ለህብረተሰቡ ግንዛቤ ማስጨበጥ ሙያዊ ሥነ ምግባርን ጠብቀው ከሚሰሩ ሚዲያዎች ይጠበቃል ነው ያሉት።

# በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ ውጤታማ የወንጀል መከላከል ስራዎች እየተሰሩ ነው

**ኤፍሬም አንዳርጋቸው**

ሐዋሳ፡- የሐዋሳ ከተማ አስተዳደር በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመታገዝ ውጤታማ የወንጀል መከላከል ስራዎችን እየሰራ እንደሆነ አስታወቀ።

የሐዋሳ ከተማ አስተዳደር ሰላምና ጸጥታ ቢሮ ኃላፊ አቶ መኩሪያ መኔሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የወንጀል ባህሪያትና መጠን በየጊዜው ተቀያያሪ መሆን የወንጀል መከላከል ስራን አድካሚ፣ ብዙ የሰው ሃይልና ሀብት የሚጠይቅ አድርጎታል።

የከተማ አስተዳደሩ ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት የከተማዋን ሰላምና ፀጥታ ለማስጠበቅ ከመንግሥት፣ ከንግዱ ማህበረሰብ፣ ከሀገር ሽማግሌዎች፣ ከሃይማኖት አባቶች፣ ከሲቪክ ማህበረሰብ፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር በቅንጅት እየሰራ ይገኛል።

በዚህም ከተማዋ የተለያዩ የስብሰባ እና የኮንፈረንስ ማዕከል በመሆን ትላልቅ ሃይማኖታዊ፣ ፖለቲካዊ ፣ መንግሥታዊ፣ የብሔር ብሔረሰቦች ቀን፣ የብልጽግና ፓርቲ ጉባዔ፣ የአደባባይ ባህላትን ያለምንም ችግር ማክበር ችላለች ብለዋል።

ይህም ከተማዋ የቱሪዝም መዳረሻና ትላልቅ አገራዊና ዓለም አቀፍ ጉባዔ ያለምንም የጸጥታ ችግር እንድታከናውን ማስቻሉን ጠቅሰው የተገኘውን ሰላምና ጸጥታ የበለጠ ለማጎልበትና መልኩን እየቀያየረ የሚከሰተውን የጸጥታ ስጋት ለመቅረፍ የከተማ አስተደዳሩ ከክልሉ እና ፌዴራል መንግሥት ጋር በመነጋገር በቴክኖሎጂ የታገዘ የወንጀል መከላከል ስራ እየሰራ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

በተለይም የደህንነት ካሜራዎቹን በከተዋማ በዋና ዋና መንገዶች፣ በክልል ተቋማት፣ በባንኮች፣ ከፍተኛ ወንጀል በሚሰራባቸው አካባቢዎች እና በመሳሰሉት ላይ እየተገጠሙ ነው።

የከተማ አስተዳደሩ ካሜራዎቹን ለማስገጠም ከ40 እስከ 50 ሚሊዮን ብር ወጪ እንደሚያደርግ ጠቅሰው፤ የደህንነት ካሜራዎቹ ከተገጠሙ ጀምሮ በከተማዋ



**አቶ መኩሪያ መኔሳ**

የሚሰሩ ወንጀሎችን ማስቀረት ተችሏል ብለዋል።

በተጨማሪም የካሜራው መገጠም ከሌላ ከተማ በተለይም ከአዲስ አበባ መኪና ሰርቆ ይዞ መምጣት፣ የሞባይል ንጥቂያ፣ የመኪና ግጭት እና ተያያዥ ወንጀሎችን በስፋት እየተከላከለ መሆኑን አብራርተዋል።

ይህንን አሰራር ሌሎች ክልሎች እና የከተማ አስተዳደሮች እንደ ምርጥ ተሞክሮ እየወሰዱት ይገኛሉ። በቀጣይም ከተማ አስተዳደሩ የደህንነት ካሜራ ገጠማውን በሁሉም ቦታ ለማዳረስ ከኢትዮ-ቴሌኮም፣ ከመብራት ኃይል እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት እየሰራ መሆኑን ገልጸዋል።

ይህም የከተማዋን ሰላምና ፀጥታ ለማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን በከተማዋ የሚደረጉ ክልላዊ ፣ ሀገራዊ እና ዓለምአቀፋዊ ጉባዔዎች እንዲሳኩና የከተማዋን የቱሪስት መዳረሻነት የበለጠ ያጠናክራል ሲሉ አቶ መኩሪያ ተናግረዋል።

# “በአገራዊ ምክክሩ ሒደት የውጭ ጣልቃ ገብነት አይኖርም”

- ዶክተር ዮናስ አዳዬ

**ጸጋዬ ጥላሁን**

አዲስ አበባ፡- በሀገራዊ ምክክሩ ሒደት የውጭ ጣልቃ ገብነት እና ጫና እንደማይኖር የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ገለጸ።

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶክተር ዮናስ አዳዬ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ለምክክር ኮሚሽኑ መንግሥት አቅም በፈቀደ መልኩ ድጋፍ እያደረገ በመሆኑ በውጭ ጫና ስር የሚወደቅበት ምክንያት አይኖርም ብለዋል።

እንደ ኮሚሽነሩ ገለጻ፤ ኮሚሽኑ ከመጀመሪያው ጀምሮ የውጭ ጫና እና ጣልቃ-ገብነት እንዳይኖርበት ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ይገኛል። ለዚህም መላ ኢትዮጵያውያን ባለቤትነታቸውን በተለያየ መንገድ እየገለጹ ናቸው። በአሁኑ ወቅት በየክልሎች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን ለመክፈትም እንቅስቃሴ ተጀምሯል።

በተፎካካሪ ፓርቲዎች፣ በሲቪክ ማኅበራት፣ በንግዱ ማኅበረሰብ፣ በዕድሮች፣ በሃይማኖት ተቋማት እና በሌሎች አማካኝነት የሚያስፈልገንን ድጋፍ ሁሉ እያገኘን ነው። ሕዝቡም ሁሉን አቀፍ ድጋፍ እንደሚያደርግና ከጎናችን እንደሚቆም በተግባር እያሳየን ነው ያሉት ኮሚሽነሩ፤ በአንዳንድ አካላት ሀገራዊ ምክክሩ ለሁሉም የኢትዮጵያ ችግሮች የመጨረሻ መፍትሄ አድርጎ ማሰብ በመሰረታዊ ሃሳብነት ችግር የለውም። ሁሉም ነገር በምክክር ቢፈታ መልካም ነበር። ነገር ግን በምክክር ቶሎ የማይፈቱ አንዳንድ ጉዳዮች ሊኖሩ ይችላሉ። ወደ ተግባር ሲተረጎም ችግሮችን በሙሉ በንግግር ብቻ ለመፍታት የምንቸገርባቸው ሁኔታዎች እንዳሉ በተግባር ባለፈው ጊዜ አይተናል ብለዋል።

ምክክሩ ሁሉንም ችግር ይፈታል የሚለው ብዥታ መጥራት አለበት። ነገሮችን በአንጻራዊነት ማየት ያስፈልጋል። ሁሉም ችግሮች በምክክር ሊፈቱ ስለማይችሉ፤ አንዳንዶቹ በጊዜ ሂደት፣ ሌሎቹ ደግሞ በሽምግልና እና በድርድር የሚፈቱ ጉዳዮች መኖራቸው ገንዛቤ ሊዝበት ይገባል ሲሉ ዶክተር ዮናስ ተናግረዋል።

የምክክሩ ዋና ዓላማ፤ ሰላምን በሰላማዊ መንገድ ማምጣት፣ የሀገሪቱ የፖለቲካዊ ባህል ማዳበር እና ለዘመናት የቆዩ ቁርሾዎችን በመሰረታዊነት በመፍታት ዘላቂ ሰላም መገንባት ነው።

አህጉራዊ ተሞክሮዎችን የገለጹት ኮሚሽነሩ፤ የየመኑ እና የሱዳኑ አገራዊ ምክክር ሂደት ያልተሳካበት ምክንያት የውጭ እና የውስጥ ጫናዎች ስለነበሩበት ነው። በሌላ በኩል የቱኒዚያው አገራዊ ምክክር ስኬታማ የሆነው ሁሉም በኃላፊነትና በአንድ ላይ ስለተንቀሳቀሰ እንደሆነ ተናግረዋል።

ዳያስፖራዎች የአገራዊ ምክክሩ አካልና ባለቤት በመሆናቸው ከእነሱም ጋር እንደሚመካከሩ ያወሱት ኮሚሽነሩ፤ ለተግባራዊነቱ ጥረታቸውን ማድረግ እንዳለባቸው መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

# በመንግሥትና በግል አጋርነት...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

የቤት ፍላጎትና አቅርቦቱን ለማጣጣም የከተማ አስተዳደሩ የተለያዩ የቤት ልማት አማራጮችን ነድፎ ወደ ስራ መግባቱን የጠቆሙት ከንቲባዋ፤ ነዋሪዎች በማኅበር ተደራጅተው እንዲገነቡ እየተሰራ መሆኑን ጠቁመዋል።

ከንቲባዋ እንደገለጹት፤ ከተማ አስተዳደሩ የቤት ፍላጐትን ለማሟላት በኮንዶሚኒየም ግንባታ፣ በቤት እድሳት እንዲሁም ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም በአጭር ጊዜ ተገጣጣሚ ቤቶችን በመገንባት ለነዋሪዎች ምቹ መኖሪያ አካባቢዎችን እየፈጠረ ይገኛል።

አስተዳደሩ በከተማዋ ያለውን ከፍተኛ የቤት ፍላጐት መንግሥት ለማሟላት ብዙ ጥረት አድርጓል። በመንግሥት ብቻ የቤት ፍላጐትን ማሟላት ስለማይቻል የግሉ ዘርፍ በቤት ግንባታው እንዲሳተፍ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር የቤት አቅርቦቱን ለማሳደግ እየተሰራ ይገኛል። የከተማ አስተዳደሩ አልሚዎቹ ለሚያከናውኑት ስራ አስፈላጊውን እገዛ እንደሚያደርግም ተናግረዋል።

የከተማ አስተዳደሩ ለቤት ልማቱ መሬት በነጻ የሚያቀርብ ሲሆን መሠረተ ልማቱንም እንደሚያሟላ ከንቲባ አዳነች አቤቤ አስታውቀዋል። በመጀመሪያው ዙር የተፈራረሙ እያንዳንዱ አልሚዎች በአማካይ ከ 1 ሺ በላይ ቤቶችን ለማልማት ጥያቄ ያቀረቡ ሲሆን፣ ግንባታውንም እስከ ሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ እንደሚያጠናቅቁ ተገልጿል።

ቤቶቹን በጥራትና በወቅቱ በመገንባት ለነዋሪዎች ማስተላለፍ እንዲቻል አልሚዎቹ በፍጥነት ወደ ሥራ እንዲገቡ ከንቲባዋ አሳስበዋል።

በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ ለሚገነቡ የ30/70 የማህበር ቤቶች ላይ ፕሮፖዛል ካቀረቡ 150 አልሚዎች 68ቱ መመረጣቸው ተመላክቷል።

የቤት አልሚዎች በበኩላቸው ከከተማ አስተዳደሩ ጋር በጋራ ቤቶችን ለመገንባት የተጀመረውን ጥረት አድንቀው ግንባታው በፍጥነትና በኃላፊነት እንደሚያካሂዱ ገልጸዋል።

በመዲናይቱ የጋራ መኖሪያ ቤት ለማግኘት ከተመዘገቡ አንድ ሚሊዮን ዜጎች ለአንድ ሶስተኛው ብቻ ማድረስ መቻሉን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስታውቋል። ለነዋሪዎች የጋራ መኖሪያ ቤት ለመገንባት በተደረገው ጥረት የከተማ አስተዳደሩ ብድር በመውሰዱ 54 ቢሊዮን ብር እዳ እንዳጋጠመው ከንቲባ አዳነች ገልጸዋል።

# በአዲስ አበባ በቂ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ማኅበራት አማካኝነት የጤፍ፣ የስንዴና የበቆሎ ምርቶች ከትናንት ጀምሮ በስፋት ማቅረብ ጀምሯል ያሉት ምክትል ፕሬዚዳንቱ፤ በከተማዋም ሆነ በሀገሪቷ በቂ ምርት አለ። ክልሉ በከተማዋ ሆን ተብሎ የምርት እጥረት ለመፍጠር የሚንቀሳቀሱ አካላትን ሴራ ለማክሸፍ ከከተማ አስተዳደሩ ጋር ባጋራ ይሰራል ብለዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ንግድ ቢሮ ኃላፊ አቶ ቢኒያም ምክሩ በኩላቸው፤ የኦሮሚያ ክልል የከተማዋን የኑሮ ውድነትን ለማረጋጋት የሚያደርገው ጥረት የሚደነቅ እንደሆነ ተናግረው፤ የግብርና ምርቶቹ ለጊዜው በሳርቤት አደባባይ የሚገኙ መሆናቸውን ገልጸዋል። ተደራሽነቱ ይበልጥ ተጠናክሮ በየክፍለ ከተሞች እንዲኖር ይደረጋል ነው ያሉት።

በከተማዋ የምርት እጥረት ለመፍጠር የሚንቀሳቀሱ አካላት ከድርጊታቸው ሊታቀቡ እንደሚገባም ያሳሰቡት የቢሮ ኃላፊው ከትናንት ጀምሮ በከተማዋ ሰፊ አቅርቦት እንዳለ ገልጸው፤ ኅብረተሰቡ በከተማው የገበያ አሻጥር የሚፈጥሩ አካላትን በማጋለጥ እንዲተባበር ጠይቀዋል።

በሌላ በኩል ጨፌ የወጣቶች መሠረታዊ ህብረት ስራ ማህበር በጅሞ አንድ የገበያ ማዕከል የጤፍ ምርትን በተመጣጣኝ ዋጋ እያቀረበ ነው። ኅብረተሰቡ ከትናንት ጀምሮ ነጭ ማኛ ጤፍ በስድስት ሺህ 800 ብር በጀሞ አንድ የገበያ ማዕከል ማግኘት እንደሚችልም የማኅበሩ ፕሬዚዳንት ገልጸዋል።

ጨፌ ወጣቶች ሁለገብ ኃላፊነቱ የተወሰነ መሠረታዊ ኅብረት ስራ ማህበር ፕሬዚዳንት ሰኘ ኢደሹ ለጋዜጠኞች እንደተናገሩት፤ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ነጭ ማኛ ጤፍ በስድስት ሺህ 800 ብር በጀሞ አንድ የገበያ ማዕከል ማግኘት ይችላል። ኅብረተሰቡ በከተማዋ በሚገኙ የኅብረት ሥራ ማኅበራት መሸጫ ቦታዎች መግዛት እንዲችሉ እንደሚደረግም ተናግረዋል።

ከሰሞኑ በተለያዩ ምክንያቶች በተለይ የጤፍ ዋጋ መናሩን ተከትሎ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የተለያዩ ዘገባዎችን ለሕዝብ ማድረሱ የሚታወስ ነው። በዚህ የዋጋ ንረት 100 ኪሎ ጤፍ እስከ ስምንት ሺህ ብር እስከ መሸጥ ደርሶ ነበር።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለግብርናው ዘርፍ የተሰጠው ትኩረት ተገቢና ለኢትዮጵያ የብልጽግና ጉዞ መሠረት የሚሆን ነው!

የግብርናው ዘርፍ ምርትና ምርታማነት እያደገ ይገኛል። በስንዴ ምርትና ምርታማነት ላይ እየታየ ያለው ለውጥ ለዚህ አንድ ሁነኛ ማሳያ ነው። ስንዴ በመኸር ብቻ ይለማ ከነበረበት ሁኔታ በበጋ መስኖ እንዲለማ በማድረግ በምርታማነቱ ላይ ትርጉም ያለው ለውጥ ማምጣት ተችሏል። በመኸር ወቅት ይገኝ የነበረው የስንዴ ምርት መጠንም እየጨመረ መጥቷል።

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የግብርናው ምርትና ምርታማነቱ እየጨመረም በዘርፉ ካለው እምቅ አቅምና የግብርና ምርት ፍላጎት ከፍተኛነት ጋር በተያያዘ የሚፈለገውን ያህል እየተመረተ አለመሆኑ በመንግሥት በኩል ታምኖበት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደጉ ሥራ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሠራበት ነው። ይህን ተከትሎም ምርትና ምርታማነቱ መጨመሩ ቀጥሏል።

የግብርናው ዘርፍ ምርትና ምርታማነት እየጨመረ ከመጣባቸው ምክንያቶች መካከል መንግሥት ለዘርፉ የሰጠው ትኩረት ይጠቀሳል፤ መንግሥት ለአፈር ማዳበሪያና ለምርጥ ዘር አቅርቦት፣ ለሜካናይዜሽን አገልግሎት እና ለኩታ ገጠም እርሻ መስፋፋትና ለመሳሰሉት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ይገኛል። ለአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት ብቻ በየዓመቱ ብዙ ቢሊዮን ብር ድጎማ እያደረገ ያለበት ሁኔታም ይህንኑ ያረጋግጣል።

መንግሥት ባለፈው የምርት ዘመን ለአፈር ማዳበሪያ ግዥ 15 ቢሊዮን ብር ድጎማ አድርጓል። ከሰሜኑ ኢትዮጵያ ጦርነት ጋር በተያያዘ በሀገሪቱ ላይ ተደርጎ በነበረው ጫና የተነሳ ማዳበሪያ የመግዛት አቅሙም እያለ የሚገዛባቸው ሀገሮች ማዳበሪያ ለኢትዮጵያ እንዳይሸጡ መደረጋቸውን ተከትሎ ብዙ ፈተናዎች አጋጥመው እንደነበርም ይታወሳል። ይሁንና መንግሥት ለግብርናው ዘርፍ ባለው ቁርጠኛ አቋም በዚያ አስቸጋሪ ወቅት ጭምር የአፈር ማዳበሪያ ገዝቶ አቅርቧል፤ በሃገር ውስጥ በተፈጥሮ ማዳበሪያ አቅርቦት ላይ በስፋት እንዲሠራም አርጓል። በዚህም የግብርናው ሥራ በማዳበሪያ እጥረት ሳይስተጓጎል ተካሂዶ የዘርፉን ምርትና ምርታማነትም ማስቀጠል ተችሏል።

መንግሥት ዘንድሮም 2015/16 የምርት ዘመን ለአፈር ማዳበሪያ ግዥ የሚውል 21 ቢሊዮን ብር ድጎማ ማድረጉን ሰሞኑን የግብርና ሚኒስትሩ አስታውቀዋል። በዚህም 12 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ግዥ ተፈጽሞ አራት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታሉ ወደ ክልሎች ተጓጉዟል። ለዚህ የምርት ዘመን ለበጋ መስኖ፣ ለበልግና ለመኸር ካለፈው ዓመት የተረፈ ማዳበሪያን ጨምሮ 15 ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ጥቅም ይውላል።

ድጎማው በየዓመቱ እየተመዘገበ ያለው የግብርናው ዘርፍ ምርትና ምርታማነት በማዳበሪያ አቅርቦት ምክንያት እንዳይስተጓጎል ለማድረግና በአርሶ አደሩ ላይ ሊኖር የሚችለውን ጫና ለመቀነስ ታስቦ የተደረገ መሆኑም ተጠቁሟል። በዋጋ አኳያም አርሶ አደሩ ባለፈው የምርት ዘመን ማዳበሪያ ይገዛበት ከነበረው ገንዘብ መጠን ጋር ተመጣጣኝ እንዲሆን ተደርጓል። በዓለም አቀፍ ደረጃ በተለያዩ ምክንያቶች ዋጋው እየጨመረ ያለው የአፈር ማዳበሪያ በአርሶ አደሩ ላይ ጫና እንዳያሳርፍ የድጎማው ፋይዳ ከፍተኛ ነው።

ሀገርና መንግሥት ከግብርናው ከሚጠብቁት ምርትና ምርታማነት መጨመር፣ የሀገር ውስጥ የግብርና ፍላጎት መሟላት፣ የግብርናው ዘርፍ በውጭ ምንዛሪ ግኝት እያስገኘ ካለው ጥቅም፣ ዘርፉ በምርትና ምርታማነት ብዙ ርቀት መጓዝ ያለበት ከመሆኑ በተለይ በስንዴ ልማት ላይ እየተከናወነ ካለው መጠነ ሰፊ ተግባር አኳያ ሲታይ የመንግሥት ድጎማ ተገቢና ለግብርናው ዘርፍ ምርትና ምርታማነት ማደግ ያለውን ቁርጠኛ አቋም አሁንም ያረጋገጠበት ነው ማለትም ይቻላል።

እንደሚታወቀው ሃገሪቱ ለእርሻ ሥራ ሊውል የሚችል ሰፊ ለም መሬት፣ ጉልበት፣ የውሃ ሀብትና አየር ንብረት ባለቤት ናት፤ ይህ ሁሌም ሲጠቀስ ኖሯል። እነዚህ ሀብቶች ብቻቸውን ግን ብዙም የፈየዱት ነገር የለም። ከእዚህ ሁሉ እምቅ ሀብት ተጠቃሚ ለመሆን እነዚህን የልማት አቅሞች አስተባብሮ መምራት፣በቴክኖሎጂ መደገፍ፣እና ምቹ ፖሊሲዎችን ወደ ሥራ ማስገባት የግድ ነው። መንግሥት እያደረገ ያለውም ይሄው ነው።

መንግሥት ግብርናው ምርትና ምርታማነት እያደገም ምርትና ምርታማነቱ የሚጠበቀውን ያህል ስለአለመሆኑና ይበልጥ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት እንዳለበት ሲያስገነዝብ ቆይቷል። ማስገነዝብ ብቻም ሳይሆን ለዘርፉ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች፣ ቴክኖሎጂዎች አቅርቦት፣ በባለሙያዎች ስምሪት ስልጠናና የመሳሰሉት ላይም በስፋት ተንቀሳቅሷል።

የአፈር ማዳበሪያ፣ ምርጥ ዘር፣ የተባይ ማጥፊያ አቅርቦት ላይ በስፋት ተሠርቷል፤ እየተሠራም ነው። በቴክኖሎጂ በኩልም ሜካናይዜሽን እንዲስፋፋ በተደረገው ጥረት በርካታ አካባቢዎች በትራክተር ማረስ፣ በኮምባይነር አዝመራ መሰብሰብና መውቃት ውስጥ የገቡበት ሁኔታ ተፈጥሯል። በበጋ ስንዴ መስኖ ልማት ለተሰማሩ አርሶ አደሮች የውሃ መሳቢያ ሞተሮች ማቅረብ ላይም በስፋት እየተሠራ ይገኛል።

ይህን ተከትሎም ከግብርናው ዘርፍ በየዓመቱ የሚገኘውን ምርት በከፍተኛ መጠን ማሳደግ እየተቻለ ነው። የበጋ ስንዴ መስኖ ልማትን አጠናክሮ በመቀጠል አርሶ አደሮች ከመሬታቸው በዓመት ከሚያገኙት ምርት በእጥፍ ብልጫ ያለው ምርት የሚያገኙበትን ሁኔታ መፍጠር እየተቻለ ነው።

ግብርናው ሲሰጡት አብልጦ ይሰጣል እንደተባለው ለግብርናው አስፈላጊውን አቅርቦት በማድረግ ግብርናው የሚፈልገውን ውጤት እንዲሰጥ ማድረግ እየተቻለ ነው። መንግሥት ዘንድሮም ለግብርናው ዘርፍ ማድረግ ያለበትን ድጋፍ አጠናክሮ መቀጠሉም ለምርትና ምርታማነቱ ቀጣይነት መሠረታዊ አቅርቦት የሰጠውን ትኩረት ያረጋገጠበት ሊባል ይችላል።

ድጎማው መንግሥት ለግብርናው ዘርፍ ምርትና ምርታማነት እድገት ቀጣይነት ያሳየው ቁርጠኝነት ተጨባጭ መገለጫ ነው። ይህ ቁርጠኝነት የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት የሚችለው የአፈር ማዳበሪያው አርሶ አደሩ ዘንድ ደርሶ ለተፈለገው ዓላማ ሲውል ነው።

ቀሪው ሥራ ማዳበሪያው ለበልግና ለመኸር እርሻ እንዲሁም ለበጋ መስኖ ልማት በወቅቱ እንዲዳረስ ማድረግ ይሆናል። ለዚህ ደግሞ ማዳበሪያውን በማጓጓዝና በማሰራጨት ከፍተኛ ሚና ያላቸው አካላት ቁርጠኝነት ወሳኝ ይሆናል። በዚህ በኩል ለአርሶ አደሮች ቅርበት ያላቸው የአርሶ አደሮች የኅብረት ሥራ ማኅበራት፣ ዩኒየኖች እንዲሁም የክልል፣ የዞንና የወረዳ የሚመለከታቸው አካላት እንዲሁም በትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ላይ የሚሠሩ ተቋማት ሚና ከፍተኛ ነው።

እነዚህ አካላት ማዳበሪያው ለየወቅቶቹ እንዲደርስ ቅንጅታዊ ርብርብ ማድረግ ይኖርባቸዋል፤ በዚህ ወቅት ቅድሚያ ሊሰጣቸው ከሚገቡ ተግባሮች መካከል አንዱና ዋናውም ይሄው የአፈር ማዳበሪያን ለአርሶ አደሩ ማድረስ ይሆናል!


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

<u>የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ</u>
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

<u>ዋና አዘጋጅ</u>
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

<u>አድራሻ</u>
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

<u>የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ</u>
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

<u>የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር</u>
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

<u>የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች</u>
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

<u>የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል</u>
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

<u>የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ</u>
ስልክ - 011-1-26-43-39

<u>ማከፋፈያ</u> :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው።በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## ዛሬ አብዝተን የምንሻው የዓድዋ ድል ኅብርና አንድነት

**ኢያሱ መሰለ**

አውሮፓውያን በ18ኛው ክፍለ ዘመን ኢንዱስትሪዎቻቸውን ባስፋፉ ማግስት ጥሬ ሀብት ለመቀራመት እና ለምርቶቻቸው ማራገፊያነት አይናቸውን የጣሉት አፍሪካ ላይ እንደነበር የታሪክ መዛግብት እና ምሑራን ያስረዳሉ። እናም የአውሮፓ አገራት በበርሊኑ ጉባዔያቸው አፍሪካን በቅኝ ግዛት የመያዝ ሴራቸውን ዶለቱ። ለዚህ ቅርምታቸው ፍኖት እንዲሆናቸውም የአፍሪካን ካርታ ከፊታቸው ዘርግተው አገራትን እንደ ቅርጫ ሥጋ በመመደብ አህጉሪቱን ተቀራመቷት።

በዚህ ወቅት ኢትዮጵያም በጣሊያን እጅ እንድትወድቅ የቅርጫው እጣ ወጥቶባት ነበር። በዚሁ ድልድል እና ሃሳባቸው መሠረትም አብዛኞዎቹን የአፍሪካ ሀገራት በቅኝ ግዛት ስር አውለው የተፈጥሮ ሀብታቸውን በዘበዙ ፤ ባርነትንም በሕዝቦች ጫንቃ ላይ ጫኑ። ኢትዮጵያ ግን በልጆችዋ የተባበረ ክንድ ሊወሯት የመጣውን ጠላት ድባቅ መትታ ነጻነቷን አስከበረች። ከራሷ አልፋ ለአፍሪካና ለመላው ጥቁር ሕዝብ ኩራት የሆነ ደማቅ ታሪክ ጻፈች። ይሄው ድልና ገድል ታዲያ በዘመናት የማይደበዝዝ ሕያው የአሸናፊነት አርነት ሆኖ ዛሬም ድረስ ይዘከራል፤ ይጠናል፤ ይተነተናል።

የዓድዋ ድል ታሪክ ብቻ ሳይሆን ሕያው የድል ሐውልት ነውና ከዛሬ የተሻገረ አስተምህሮ እንዲኖረው፤ ለነገው ትውልድ ስንቅና አቅም እንዲሆን በምሑራን በርካታ ሥራዎች እየተከናወኑም ይገኛሉ። የአዲስ አበባው የዓድዋ ፓርክ ፕሮጀክት የዚህ አንድ ማሳያ ሲሆን፤ በየዩኒቨርሲቲዎች የሚከናወኑ መድረኮችና በምሑራኑም የሚሰጡ አስተያየቶች፤ እንዲሁም የጥናት ሥራዎችም በርካታ ናቸው። የታሪክ ምሑራን እና ተመራማሪዎች ደግሞ ይሄንን ታሪክ በሚገባ አጥንቶና ሰንዶ ከማኖር አኳያ የማይተካ ሚና አላቸው።

በጂማ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ መምህርና ተመራማሪ ዶክተር ከተቦ አብዲዮ፤ የዓድዋን ጦርነት መንስዔ እና ውጤት እንዲህ ያስረዳሉ። በበርሊኑ ጉባኤ ውሳኔና እጣቸው መሠረት ጣሊያኖች ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት ለመያዝ አስበው እኤአ በ1885 በእንግሊዞች ትብብር እግራቸውን ምፅዋ ላይ አሳረፉ። ቀስ በቀስ ከምፅዋ ወደ ዶጋሊ፣ ከዚያም ወደ ሰሐሊን ግዛታቸውን ማስፋፋት ጀመሩ።

ነገር ግን በወቅቱ የነበሩት ንጉሥ አጼ ዮሐንስ ጣሊያኖቹ እንደፈለጉት እንዲሆኑ እድል አልሰጧቸውም ነበር። አጼ ዮሐንስ ከደርቡሾች ጋር ባደረጉት ጦርነት በክብር መሰዋታቸውን ተከትሎ ግን ጣሊያኖች ከሰሜን ወደ ደቡብ ለሚያደርጉት መስፋፋት አመቺ ሁኔታ ተፈጠረላቸው።

ወቅቱ ደግሞ ገና አፄ ምኒልክ ንግሥናቸውን ለዓለም ማኅበረሰብ እያሳወቁ የነበረበት በመሆኑ ጣሊያኖች ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ለአፄ ምኒልክ እውቅናና ድጋፍ እንደሚሰጧቸው በማስመሰል የስምምነት ውል መፈራረም እንዳለባቸው ያሳምኗቸዋል። በውጫሌው ስምምነት የአፄ ምኒልክን መንግሥታዊ መዋቅር ይደግፋሉ በሚል 20 አንቀጾችን ጽፈው ከንጉሡ ጋር ይፈራረማሉ።

ይሁን እንጂ ይህ ስምምነት በውስጡ የኢትዮጵያን ክብርና ሉዓላዊነት የሚጻረር ሃሳብን በውስጡ የያዘ በመርዝ የተለወሰ ማር ዓይነት ነበረ። በተለይም በአንቀጽ 17 ላይ የሰፈረው ሃሳብ የዚህ አብይ ማሳያ፤ ወደማይቀረው ጦርነት የመራ መርዛማ ሃሳብን የያዘ ነበር። ምክንያቱም አንቀጹ በተለይ በኢጣሊያንኛ ትርጉሙ የኢትዮጵያን ክብርና ሉዓላዊነት የሚጻረርና ኢትዮጵያ ለኢጣሊያ ተገዥ መሆኗን የሚገልጽ ነበር።

ሆኖም ይህ እውነት በጥሞና ከተጤነና የትርጉሙ መዛባት ከታወቀ በኋላ በንጉሡና በመኳንንቱ ዘንድ ቁጣን ያስነሳል። ጣሊያኖችም ውሉን ከማስተካከል ይልቅ በኢትዮጵያ ጉዳይ ከእኛ በላይ የሚመለከተው የለም በሚል እንደፈለጋቸው ሊፈነጩ ሞከሩ። በማንአለብኝነት የያዙትን ቦታም ማስፋፋት ጀመሩ፤ መረብ ወንዝን ተሻግረው መቀሌ፣ አምባላጌ ፣ ማይጨው እያሉ ወደ መሐል ሀገር እየተንሰራፉ መጡ። ይሄን የተገነዘቡት ንጉሥ አፄ ምኒልክ እና ሹማምንቶቻቸውም ከመከሩ በኋላ ውሉን ከመሰረዝ ባሻገር የሀገርን ክብር ለማስጠበቅ ወደሚችሉበት ርምጃ መሸጋገር የግድ መሆኑን ወሰኑ።

### ጥሪ እና ምላሽ

በወቅቱ የጣሊያኖች ተግባርና ጉዞ የገባቸው ንጉሡ፣ አገር የማስጠበቅ ኃላፊነት አለባቸውና ስለ ወራሪው ባሕሪ በመግለጽ እና ሁሉም ይሄን ወራሪ የመከላከል ሁለንተናዊ ግዴታ እንዳለበት በማሳሰብ አዋጅ አስነገሩ። «... አገር የሚያጠፋ ሃይማኖት የሚለውጥ ጠላት እግዚአብሄር የወሰነልንን የባሕር በር አልፎ መጥቷልና እኔም የአገሬን ከብት ማለቅ የሰውን መድከም አይቼ እስከ አሁን ዝም ብለው ደግሞ እያለፈ እንደፍልፈል መሬት ይቆፍር ጀመር....»......«.....አሁን ግን በእግዚአብሔር ረዳትነት ሀገሬን አሳልፌ አልሰጠውም። የሀገሬ ሰው ከአሁን ቀደም የበደልሁህ አይመስለኝም። አንተም እስከ አሁን አላስቀየምከኝም። ጉልበት ያለህ በጉልብትህ እርዳኝ። ጉልበትም የሌለህ ለልጅህ ለምሽትህ ለሃይማኖትህ ስትል በኀዘን እርዳኝ። ወስልተህ የቀረህ ግን ኋላ ትጣላኛለህ አልተውህም። ማርያምን ለዚህ አማላጅ የለኝም። ዘመቻዬ በጥቅምት ነውና የሸዋ ሰው እስከ ጥቅምት እኩሌታ ድረስ ወረይሉ ከተህ ላግኝህ። » (አፄ ምኒልክ እና የኢትዮጵያ አንድነት፣ ተክለ ጻዲቅ መኩሪያ፣ ገጽ ፤226)

ከ127 ዓመት በፊት የታወጀው ይህ የክተት አዋጅ፣ የኢጣሊያ መንግሥት ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት ለማንበርከክ በሰሜን የሀገራችን ክፍል የያዛቸውን ግዛቶች እያስፋፋ ወደ መሐል ሀገር ሲገሰግስ የኢትዮጵያ ሕዝብ በወራሪው ጠላት ላይ ክንዱን አስተባብሮ የማያዳግም ርምጃ በመውሰድ የሀገሩን ዳር ድንበር እንዲያስከብር አቅም የሆነው ነበር። ይሄ የንጉሡ ሀገር አላስደፍርም የክተት ጥሪ እና ከሕዝቡ የተሰጠው ምላሽ ድምር ውጤትም ዛሬ ኢትዮጵያ በድልና አርነት ከፍ ብላ እንድትገለጥ ያደረጋት ስለመሆኑም፤ ከዚህም በላይ ኢትዮጵያውያን መሪና ተመሪዎች የነበራቸውን ኅብረትና መናበብ በእጅጉ ከፍ አድርጎ ያሳያ እንደነበር ነው በርካቶች የሚመሰክሩት።

ዶክተር ከተቦ፣ ስለ አዋጁ እና ለንጉሡ የክተት የአዋጅ ጥሪ ሕዝቡ የሰጠውን ምላሽ እንዲህ ይገልጻሉ። አጼ ምኒልክ ምታ ነጋሪት ክተት ሠራዊት ብለው ሲያውጁ ለጋራ አገራቸው ቀናዒ የሆኑት የኢትዮጵያ ሕዝቦች ጥሪውን ተቀብለው በነቂስ ወጥተዋል። የትግራይ ፣ የበጌምድር፣ የጎጃም ፣ የወሎ፣ የዋግ፣ የሸዋ ፣ የሐረር እና በአራቱም የኢትዮጵያ ማዕዘናት ያሉ መሳፍንቶችና ሀገረ ገዢዎች በርካታ ተዋጊዎቻቸውን በመያዝ የአጼ ምኒልክን ጥሪ ተቀብለው ወደ ዓድዋ ዘምተዋል።

ከብዙ በጥቂቱ ለመጥቀስ ያህልም፣ የወላይታው ንጉስ ካዎ ጦና ፣ የጂማው አባጂፋር፣ የወለጋው ኩምሳ ሞረዳ፣ ሼኮ ጄላል ሀሰን፣ የቄለም

ወደ6ኛው ገጽ ዞሯል

# ነፃ ሃሳብ

# ዛሬ አብዝተን...

ከ5ኛው ገጽ የዞረ

ወሊጋው ጆቴ ቱሉ፣... የመሳሰሉት ተዋጊዎቻቸውን በመያዝ ለጥሪው ምላሽ ሰጥተዋል። ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ፣ከሰሜን እስከ ደቡብ ያሉ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ከየአካባቢያቸው በወጡ ጦር መሪዎች ሥር ታቅፈው በጦርነቱ መሳተፋቸውን ዶክተር ከተቦ ይናገራሉ።

እነዚህ ገዢዎችና ነገሥታት የንጉሡ ነገሥቱን ጥሪ ተቀብለውና ጦራቸውን አሰልፈው ለእናት ሃገራቸው ክብር ሲዘምቱ ዘር፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ የፖለቲካ አመለካከት አልለያያቸውም። ሌላው ቀርቶ ከንጉሡ ጋር የተኳረፉና የሸፈቱ ሳይቀሩ ንጉሡን ይቅርታ እንዲያደርጉላቸው እየጠየቁ የጋራ ጠላታቸውን ለመዋጋት ተሰልፈው ተዋድቀዋል። ሕዝቡ የመደጋገፍና የአንድነት ስሜቱ ከፍተኛ ስለነበርም፤ ስንቁን እያዘጋጀ ወደ ግንባር ለመትመምም ጊዜ እንዳልፈጀበት ነው የታሪክ ምሑሩ ያስረዱት።

አባጂፋር፣ ካኦ ጦና እና ኩምሳ ሞሮዳ ወታደሮቻቸውን ይዘው ወደ ዓድዋ እየተንቀሳቀሱ በነበረበት ወቅት፣ አጼ ምኒልክ ሁሉም አገረ ገዢ ተዋጊውን ይዞ ወደ ሰሜን ከሄደ መሐል ሀገሩ ባዶውን እንዳይቀር በሚል ከፊል ወታደሮቻቸውን ብቻ እንዲልኩና እነርሱ ቀሪዎቹን ይዘው አዲስ አበባንና አካባቢያቸውን እንዲጠብቁ ማድረጋቸውን ዶክተር ከተቦ ተናግረዋል።

በተመሳሳይ መልኩ የወቅቱን የክተት ጥሪ ጉዞ በተመለከተ በተለያዩ መጽሐፍት እና ሰነዶች ተከትበው ይገኛሉ። « ....አጼ ምኒልክ ይህን አዋጅ በመስከረም ወር ካስነገሩ በኋላ እርሳቸው ጥቅምት 2 ቀን 1888 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ወደ ዘመቻው ተጓዙ፤... የክተት አዋጁ ከታወቀ ወዲህ የጎጃም የቤጌምድር የወሎና የላስታው ከ300 እስከ 500 ኪሎ ሜትር፤ የሸዋ የሐረር፣ የባሌ፣ የአርሲ፣ የከንባታ፣ የሲዳማ የጂማ የከፋ፣ የወሊጋና የኢሉባቦር ጦር ከ600 መቶ እስከ 1000 ወይም እስከ 1500 ኪሎ ሜትር ወደ ጦር ግንባር በእግሩ ተጉዟል፤"(ተክለጻዲቅ መኩሪያ፣ አፄ ምኒልክ እና የኢትዮጵያ አንድነት፣ (1983) ገጽ 227)።

ጳውሎስ ኞኞ ፤ አጤ ምኒልክ (1984) በሚለው መጽሐፋቸው ከገጽ 162-163 ፤ የአፄ ምኒልክን ጥሪ ተቀብለው ወደ ዓድዋ የተመሙትን ኢትዮጵያውያን አስመልክቶ ፓውሌቲ የተባለ ጸሐፊ በማሳያነት በማንሳት የውጭ አገር ጸሐፊዎች እንደሚከተለው መግለጻቸውን አስፍረዋል። «.... ሲጓዙ በደንብ ተመልክቻለሁ ዳገቱን ሲወጡ፣ ቁልቁለቱን ሲወርዱ፣ ሸለቆውን ሞልተው ሲሄዱ፣ እየተጯጯሁ ነው፤ ለወጊያ የሚሄዱ አይመስሉም። ተዋጊዎች ብቻ አይደሉም። ሴቶች፣ ሽማግሌዎች፣ አንካሶች፣ ሕጻናት፣ ቄሶች፣ አልቀሩም፤ በአንድነት ይጓዛሉ። ለጦርነት የሚሄዱ የጦር ወታደሮች አይመስሉም ነበር፤ ሕዝቡ በሙሉ ተነቅሎ ለወረራ የሚሄድ ይመስላል፤» በማለት ነበር ያሰፈሩት።

ሞልቴዶ የተባለው ጸሐፊ አጣቅሰው ባሰፈሩት መሠረት ደግሞ «...አህያው፣ በቅሎው፣ ፈረሱ፣ ሰው ሁሉ በአንድነት ይጓዛል፤ መንገዱ ሲጠብ መንገድ ይሠራሉ፤ በአንድ ጊዜ በግራ ወይም በቀኝ ይሠማሩና የጠበበውን መንገድ ይሠራሉ። ሠራዊቱ ባለፈበት መንገድ የእርጥብ ሳር ዘር እንኳን አይገኝም፤ ምክንያቱም በመቶ ሺ የሚቆጠር እግር ረግጦ ስለሚያቦነው ነው፤» ብለዋል።

ከተጓዦቹ መካከል በሺዎች የሚቆጠሩ መንገድ ሠሪዎች እና አዝማሪዎች ይገኙበታል። አዝማሪዎቹ ግጥም እየገጠሙና እያዜሙ ተጓዡን ያበረታቱት እንደነበር ተጠቅሷል። ለእንጀራ መጋገሪያ የሚሆን የሸክላ ምጣድ እና ለወጥ መሥሪያ የሚሆኑ ድስት የሚሠሩም ነበሩ። ከዚህ የምንረዳው የክተት አዋጁ የጾታ፣ የሙያ፣ የማዕረግ ፣ የብሔር ወዘተ ልዩነት ያልነበረውና ተሳትፎውም በጥሪው ልክ ሁሉንም ያሳተፈ መሆኑን ነው።

**ለጥቅም ያልተገዛ ጽኑ ኢትዮጵያዊነት**

ኢትዮጵያውያን ጥሪውን ተከትለው በአንድነት መትመም ብቻ ሳይሆን፤ ከጠላት በኩል የሚቀርብን የማታለያና መደለያ ከሀገር ክብርና ፍቅር እንደማይበልጥ ያሳዩበትን ከፍ ያለና የጸና ኢትዮጵያዊነት ያረጋገጡበት ነበር። ይሄን ሐቅ በተመለከተ ዶክተር ከተቦ እንደሚናገሩት፤ ኢጣሊያኖች ከንጉሡ ጋር ቅሬታ አላቸው የሚሏቸውን የተለያዩ አካባቢዎች ሀገረ ገዢዎች ከጎናቸው ለማሰለፍ ጥረት አድርገው ነበር። ሀገር ገዢዎቹ ግን በኢጣሊያኑ ድለላ ሳይታለሉ በዚያ ክፉ ቀን ለሀገራቸው ያላቸውን ጽኑ ታማኝነት ከንጉሡ ጎን በመቆም አረጋግጠዋል።

ጳውሎስ ኞኞ፣ አፄ ምኒልክ በሚለው መጽሐፋቸው ገጽ 164 ላይ እንዳሰፈሩትም፣ «ወራሪውን የጣሊያን ሠራዊት ለመውጋት ወደ ትግራይ ከመዘመቱ በፊት አብዛኛው የኢትዮጵያ መኳንንት በኢጣሊያ ሰርጎ ገብ ሰላዮች ስብከት ተጠምዶ ነበር። አውግስቶ ሳልምቢኒ ጎጃም ውስጥ ተቀምጦ የንጉሥ ተክለሃይማኖት ረዳትና አማካሪ በመምሰል ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ከጣሊያ ጋር ቢያብሩ የኢጣሊያ መንግሥት ባላንጣቸውን ምኒልክን ጥሎ እሳቸውን እንደሚያነግሳቸው እየነገረ ልባቸውን ይጎትት ነበር።...

...በትግራይ በኩል ጂያኮም ናሬቲ እና ሌሎችም በአጤ ዮሐንስ ጊዜ የዮሐንስ ቤተመንግሥት ባለሟል የነበሩትና የምኒልክ ባለሟል የነበረው አንቶሌኒ አጤ ዮሐንስንና ንጉስ ምኒልክን ነገር እየጎነጎኑ ሲያጣሉ እንደነበሩት ሁሉ፤ በአሁኑም ዘመን አጤ ምኒልክ ዙፋኑን የያዙት በግፍ መሆኑን ለራስ መንገሻ በመንገር ራስ መንገሻ ከኢጣሊያ ጋር ቢተባበሩ በግፍ የተወሰደባቸውን የአባታቸውን ዘውድ አስመልሰው በዮሐንስ ዙፋን ላይ እንደሚያስቀምጧቸው ቃል በመግባት እስከ ማስከዳት ደርሰው ነበር።..." የሚለውን ሰፍሮ እናገኘዋለን።

ይሁን እንጂ በዚህ መልኩ ሲሰበኩና የማይጨበጠውን የዙፋን ወራሽነት ቃል ሲገባላቸው የነበሩ እነዚህ አገረ ገዢ ኢትዮጵያውያን ግን፤ በጥቅም ሳይደለሉ ከአፄ ምኒልክ ጋር በመቆም ለዓድዋ ድል ድምቀት የራሳቸውን አስተዋጽኦ ማበርከታቸው በመጽሐፉ ተጠቅሶ ይገኛል።

ምኒልክ ህዳር 24 ቀን 1888 ዓ.ም መርሳ ላይ ሰፍረው በነበረ ጊዜ፣ ደጃዝማች ጓንጉል የሚባሉና ከአፄ ምኒልክ ጋር ተቀያይመው የሸፈቱ ሰው፤ ከንጉሡ ጎን ቆመው ጣሊያንን ለመዋጋት ተከታዩን መልዕክት ልከው እንደነበር ተጠቅሷል። መልዕክታቸውም፣ «ጃንሆይ ከእርሶ ተጣልቼ በርሃ ገብቻለሁ። አሁን ግን በሀገሬ ላይ የውጭ ጠላት ስለመጣባት የእርስዎ እና የእኔ ጉዳይ ቀርቶ ይማሩኝና መጥቼ ከእርሰዎ ከጌታዬ ጋር ሆኜ ያገሬን ጠላት ልውጋ" የሚል ነበር። ይሄ መልዕክት የደረሳቸው አፄ ምኒልክም ተደስተው እንዲመጡ አደረጓቸው፤ ደጃዝማች ጓንጉልም መጥተው ከአፄ ምኒልክ ጋር ሲገናኙ ሠራዊቱና መኳንንቱ እጅግ በጣም ደስተኛ እንደሆኑ በመጽሐፉ ተገልጿል።

**ችግሮችን በሰላም የመፍታት ጥረቶች**

ኢትዮጵያውያን በዚህ መልኩ የተጎናጸፉትን ድል ወዳረጉበት ጦርነት ከመግባታቸው በፊት፤ የተፈጠሩ ችግሮችን በሰላምና በንግግር ለመፍታት ብርቱ ጥረት አድርገው እንደነበር ድርሳናት ይጠቁማሉ። ይሄን በተመለከተ የታሪክ ምሑሩና ተመራማሪው ዶክተር ከተቦ እንደሚያስረዱት፤ አፄ ምኒልክ የክተት አዋጅ ካደረጉ በኋላም ቢሆን ተንደርድረው ወደ ጦርነት ከመግባታቸው በፊት ጣሊያኖች ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ ሰላማዊ ንግግሮችን ለማድረግ ጥረዋል፤ በዚሁ ጉዳይ ላይም በርካታ ደብዳቤዎችን ተጻጽፈዋል። ጣሊያኖች ግን የታጠቁትን ዘመናዊ የጦር መሣሪያና የሰለጠነ ወታደር ተማምነው ኢትዮጵያን በጉልበት

**ይህ ጣፋጭ ድል ኢትዮጵያውያን በተባበረ ክንዳቸው ያስመዘገቡት ታሪክ ነው። ድሉ ከሃገሬው ሰው አልፎ በባርነት ቀንበር ሥር ላሉ ጥቁር ሕዝቦች ሁሉ ተስፋን ፈንጥቋል። የዚህ ታላቅ ድል ምስጢር ምንድን ነው? በሚል ለጠየቀም፤ የታሪክ ተመራማሪዎች ምላሽ፤ በወቅቱ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ያሳዩት አንድነት፣ ጀግንነት፣ ታማኝነት፣ ቆራጥነትና አገር ወዳድነት ስለመሆኑ ያስረዳሉ**

ማንበርከክ ስለፈለጉ አፄ ምኒልክ የሚከተሉትን የዲፕሎማሲ መንገድ እንደፍርሃት ይቆጥሩት ነበር።

አፄ ምኒልክ ብቻም ሳይሆኑ፣ራስ መኮንን በግላቸው አላማጣ ላይ ተቀምጠው የኢጣሊያንን መስፋፋት በትኩረት እየተከታተሉ በነበረ ጊዜ፤ በተደጋጋሚ ለጣሊያን የጦር አመራሮች የሰላም ጥሪ ማድረጋቸውን ተክለጻዲቅ መኩሪያ አፄ ምኒልክና የኢትዮጵያ አንድነት በሚለው መጽሐፍ ገጽ 277 ላይ ጠቅሰዋል።

ይሁን እንጂ ኢጣሊያኖች የሰላም ንግግሩን አሻፈረኝ በማለት አምባላጌ ላይ መሽገው በኢትዮጵያ ወታደሮች ላይ ተኩስ ሲከፍቱ የፊት አውራሪ ገበየሁ ጦር ምሽጋቸውን ሰባብሮ ወደ መቀሌ እንዲያፈገፍጉ አድርጓቸዋል። የኢትዮጵያ ሠራዊት እግር በእግር እየተከታተለ መቀሌ የመሸገውን የኢጣሊያ ጦር ከቦ በንግሥት ጣይቱ ትእዛዝ ሰጪነት ለመጠጥነት የሚጠቀምበትን የምንጭ ውሃ በቁጥጥር ስር ያውለዋል። ይህን ጊዜ የጣሊያን የጦር አዛዦች የተከበበውን ጦራቸውን ለማዳን ሲሉ ሰላማዊ ንግግር የማድረግ ፍላጎት እንዳላቸው ይገልጻሉ።

አፄ ምኒልክ ሀሳባቸውን በመቀበል ሰው ሳይጎዳ የተከበበው የኢጣሊያ ጦር በሰላም ወደ ወገኑ እንዲቀላቀል ይፈቅዳሉ። አምባላጌ ላይ የተጀመረው ጦርነት በኢትዮጵያ ሠራዊት ድል አድራጊነት ከተጠናቀቀ እና መቀሌ የመሸገው የጠላት ጦር ከተከበበ በኋላም ቢሆን አፄ ምኒልክ የኢጣሊያ መንግሥት እየተከተለ ያለው አካሄድ ትክክል አለመሆኑን እና አለመግባባቱን በንግግር ለመፍታት ከፍተኛ ፍላጎት የነበራቸው ቢሆንም፤ በተቃራኒው ኢጣሊያኖች በሰላማዊ መንገድ የመነጋገር ፍላጎት ያላቸው በመምሰል የተከበቡ ጦራቸውን ካስለቀቁ በኋላ ጦራቸውን ወደ ዓድዋ ተራሮች በማስጠጋት ኃይላቸውን አደራጅተው ለጦርነት መዘጋጀታቸውን የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ።

**ለጣፋጭ ድል ያበቃ በኅብር ያጌጠ አንድነት**

ይህ ጣፋጭ ድል ኢትዮጵያውያን በተባበረ ክንዳቸው ያስመዘገቡት ታሪክ ነው። ድሉ ከሃገሬው ሰው አልፎ በባርነት ቀንበር ሥር ላሉ ጥቁር ሕዝቦች ሁሉ ተስፋን ፈንጥቋል። የዚህ ታላቅ ድል ምስጢር ምንድን ነው? በሚል ለጠየቀም፤ የታሪክ ተመራማሪዎች ምላሽ፤ በወቅቱ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ያሳዩት አንድነት፣ ጀግንነት፣ ታማኝነት፣ ቆራጥነትና አገር ወዳድነት ስለመሆኑ ያስረዳሉ። የዓድዋ ድል የተገኘው መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለአፄ ምኒልክ የክተት ጥሪ ምላሽ ለመስጠት በነቂስ በመውጣቱ፣ በአንድነት በመቆሙ፣ በቆራጥነት በመዋደቁ እና በጀግንነት በመሰዋቱ እንደሆነ አስረግጠው ይገልጻሉ።

የታሪክ ድርሳናቱም ቢሆኑ፤ የንጉሡ የክተት ጥሪ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በቻለው መንገድ የዘመቻው ተባባሪ እንዲሆን የሚጠይቅ ከመሆኑም በላይ፤ በኢትዮጵያውያን ፈጣን ምላሽምና በኅብረት የትግል ውጤት የተገኘን ለወገን የጣፈጠ፣ ለጠላት ግን የመረረ ስለመሆኑ ይመሰክራሉ።

እናም ዓድዋ ሲታሰብ የኢትዮጵያውያን አሸናፊነት ብቻ ሳይሆን፤ የአሸናፊነት ጉዞውና ሥራው ምስጢርም አብሮ ይወሳል። የኢትዮጵያ ሕዝብ በመደጋገፍና በመተባበር በወራሪው ጠላት ላይ ብርቱ ክንዱን አሳርፎ ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን አፍሪካን እና መላው ጥቁር ሕዝብን ያኮራ ድል የተጎናጸፈበት ስለመሆኑም ይተረካል። የዓድዋ ድል ኢትዮጵያውያን በቋንቋ፣ በዘር፣ በአመለካከት፣ በሃይማኖት፣ በአካባቢ ግዛት ሳይለያዩ በአንድ ሀሳብ በአንድ ልብ ሆነው የጋራ ጠላቶቻቸውን ለማጥፋት የየራሳቸውን አስተዋፅዖ ያበረከቱበት ታላቅ ዐውድ ስለመሆኑ ለዛሬው ትውልድ አስተማሪ ሆኖ ይገለጣል።

ተዋግተው በክብር የተሰዉ እና የቆሰሉ ጀግኖች፣ ምግብ ሲያበስሉ የነበሩ እናቶችና ስንቅ አቀባዮች፣ ቁስለኞችን የሚያነሱና የሚንከባከቡ፣የሞቱትን የሚቀብሩ ደጀኖች፣ መጋዣ የሚያቀርቡና ቀለብ የሚሰፍሩ አርሶ አደሮች፣ የመሐሉን አገር ደህንነትና ሰላም ሲያስጠብቁ የነበሩ ባለ አደራዎች፣ መንገድ ጠራጊዎች፣ በፀሎት ሲራዱ የነበሩ የሃይማኖት አባቶች፣ በዘፈንና በቀረርቶ ሞራል ሲሰጡ የነበሩ ከያኒዎች፣ ሌላው ቀርቶ የመጓጓዣ አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩ እንስሳት ሳይቀሩ የድሉ ባለቤቶች ናቸው።

ዛሬም ከዓድዋ ዘመን ከእኛ አባቶች ልንማርና ልንወስድ የሚገባን ይሄንን ነው፤ ሳይነጣጠሉ መቆምን፤ ተባብሮ ሊያጠፋና ሊበትን የመጣ ጠላትን መታገልን፤ በኅብር ደምቆ የሀገር ኩራትና ጌጥ መሆንን፤ የትናንት አባቶች ልጆችና የልጅ ልጆች ሆኖ የሀገር አንድነትና ሉዓላዊነትን በማንኛውም ዋጋ ማጽናትን፤ ለግል ጥቅም፣ ለቡድን ፍላጎት፣ ለፖለቲካዊና ሌላም ጉዳዮች ያልተንበረከከ ጽኑ ኢትዮጵያዊ ማንነትን መገንባትን፤... ከዓድዋ ባለቤቶች ልንቀስም፣ ገንዘባችን አድርገንም ልንጠቀምበትና ለኢትዮጵያችን ሁለንተናዊ ብልጽግናና ከፍታ ልናውለው ይገባል። ምክንያቱም ዛሬያችን የትናንቱን በዓድዋ መድረክ የተገለጠ በኅብር የተንቆጠቆጠ የአንድነት ገድልና ድል አብዝቶ ገንዘባችን እንድናደርግ ይሻል።

# የሲዳማ ብሔረሰብ ማህበራዊ አኗኗር እና የመረዳዳት ባህል

ማህሌት አብዱል





ኢትዮጵያ የበርካታ ብሔረሰቦችና ቋንቋዎች ባለቤት የመሆኗን ያህል በውስጧ ለዘመናት በጠንካራ ማህበራዊ ትስስር የተጋመደ ሕዝብ ያለባት አገር ነች።ይህ ማህበራዊ ትስስርና ማህበራዊ የአኗኗር ዘይቤ ታዲያ ሕዝቡ ባህሉን፤ ወጉንና ልምዱን ጠብቆ ለማቆየት ካበረከተው ፋይዳ ባሻገር ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን በመፍታት ረገድ ወሳኝ ሚና ሲጫወት ቆይቷል።ማህበራዊ እሴቱን ጠብቀው ካቆዩና አሁንም ድረስ ማህበራዊ አደረጃጀቶችን ለትውልድ ጥቅም ካሻገሩ የኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል የሲዳማ ሕዝብ አንዱ ነው። በዛሬው የሀገርኛ አምዳችንም የዚህን ማህበረሰብ ማህበራዊ አደረጃጀትና ይህንን አደረጃጀት በመጠቀም የሚከናወነው ባህላዊ ቤት አሠራር ሥርዓትና የአኗኗር ዘይቤን ለመዳሰስ እንሞክራለን፡፡

የሲዳማ ብሔረሰብ አቋም እንደማንኛውም ኅብረተሰብ ጠንካራ ማህበራዊ መስተጋብር የሚታይበት ነው።በጣም ቀላል ካልሆነ በስተቀር ማንኛውንም ሥራ በህብረት ይሠራል።ቀላል ሥራ ቢሆን እንኳን ማህበረሰቡ ‹‹ዴ›› እያለ በሚጠራው በደቦ ሥርዓት አማካኝነት ነው የሚሠራው። አቶ ከቤታና ሆጤሶ የተባሉ ጸሐፊ ‹‹የሲዳማ ሕዝብና ባሕሉ›› በሚል ርዕስ 1983 ዓ.ም ላይ ባሳተሙት መጽሐፋቸው ላይ እንደገለፁት፤ ‹‹ዴ›› ማለት በዘመዳሞች ወይም በጓደኛሞች ማለትም በቅርበት ከሚተዋወቁት መካከል በደቦ፤ በፈቃደኝነትና በፍቅር የሚሠራ ሥራ ነው። በ‹‹ዴ›› የሚሠራው ሥራ ዓይነት ቁፋሮ፣ አረማ፣ ዘር መዝራትና አጨዳ የመሳሰሉት ናቸው።ከዚህ ከፍ የሚሉ ድርጅቶች ግን በ‹‹ሴራ›› (በሕግ) የሚቋቋሙ ሲሆን ‹‹ጭናንቾ›› እየተባለ በሚጠራው ጎጥ እና ‹‹አላ›› በተባለው የቀበሌ አደረጃጀት የሚደራጁ ናቸው።

**ጭናንቾ**

በሲዳምኛ ‹‹ሴራ›› ማለት ሕግ ማለት እንደሆነ የሚጠቅሱት ጸሐፊው፤ በአንፃሩ እነዚህ ‹‹ጭናንቾ›› በመጠን ከአላ ያነሰ ንዑስ ማህበራዊ አደረጃጀት መሆኑን እንዲሁም ‹‹አላ›› በስፋቱ ከፍ ያለና የቀበሌን ያህል በቁጥር ከፍ ያለ ሕዝብ ወይም አካባቢን የሚያካትት ማህበራዊ አደረጃጀት መሆኑን ያብራራሉ። ሁለቱም አደረጃጀቶች ግን በኅብረተሰቡ ሕግ መሠረት የተደራጁ ስለሆኑ በአካባቢው የሚገኝ ለአቅመ-አዳም የደረሰ ወንድ ሁሉ በእነዚህ ድርጅቶች በግድ መካፈል የሚኖርበት መሆኑን ያስረዳሉ። ‹‹የጭናንቾ›› ተግባር ቤቶችን (መኖሪያ ቤቶች) መሥራት መሆኑን ገልፀውም፤ ‹‹በዚህ ድርጅት ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም አባል ቤቱ ቢበላሽበት ለማሠራት ሙሉ መብት አለው፤ ለዚህ ደግሞ ድርጅቱን የሚመሩ ሁለት ሰዎች ይኖራሉ›› ይላሉ። መሪዎቹም በሲዳምኛ ‹‹ሙርቻ›› የሚባሉ መሆኑን አመልክተው እነርሱም ሙሉ አባላት ባሉበት ዋና እና ረዳት በመሆን በድምፅ ብልጫ የሚመረጡበት ሥርዓት መኖሩን ያብራራሉ።

እንደእርሳቸው ገለጻ፤ ቤት ለመስራት የሚፈልግ ሰው ሄዶ ለ‹‹ሙርቻ›› ዎቹ (ለመሪዎቹ) ይነግራል።እነርሱም ለመላው አባላት ያስታውቃሉ።ሕዝቡም ውጣ በተባለው ቀን ወጥቶ ቤቱን ሠርቶ ለባለቤቱ ያስረክባል።ለሥራ በሚወጡበት ጊዜ በታዘዙበት መሠረት ጥቂት ጠርብና ማገር ይዘው ያመጣሉ። ቤት ለማሠራት ቀደም ብሎ ለጠየቀው ሰው መጀመሪያ ይሠራለታል።ቤቱ ሲሠራ ‹‹ሙርቻ›› በደንብ ይቆጣጠራል።ሥራው ሲበላሽ አፍርሶ እንደገና እንዲሠራ ያደርጋል። የማይታዘዝ ሰው ቢኖር በደንቡ መሠረት ይቀጣል። ቅጣቱም የሚወሰነው በሙርቻና በሽማግሌ ነው። የተወሰነበትን ቅጣት የማይቀበል ሆኖ ቢገኝ ለመላው የድርጅቱ አባላት ፊት ቀርቦ የተጣለበት መቀጫ ትክክል ከሆነ እንዲከፈል ይገደዳል።ይህንን የማይፈፅም ከሆነ ከድርጅቱ እንዲወገድ ይሆናል። ማንም ሰው ከድርጅቱ ወደተወገደው ሰው ቤት አይገባም፤ ከማንም ጋር ቡና ሊጠጣ አይችልም።ቢታመም እንኳን የሚጠይቀው ሰው የለም።ቢቸገር የሚደርስለት ሰው አይኖርም፣ ከእቤት እሳት ቢጠፋ ከአካባቢው እሳት ሊወስድ አይችልም።ክብሪት በሌለበት ዘመን ከጎረቤት እሳት ማጣት ምንኛ ከባድ እንደሆነ ለመገመት አያዳግትም።

ሌላው ይቅርና የተጣለበትን መቀጫ ሳይከፍል ይህ ድርጅት (ጭናንቾ ወይም አላ) በድሎኛል ብሎ በሌላ ድርጅት ውስጥ ሄዶ እንዲገባ የማይፈቀድለት መሆኑን ጸሐፊው ይገልፃሉ። ድርጅቱን ለቆ ለመውጣት ቢፈልግ መጀመሪያ የተጣለበትን መቀጫ መክፈል የሚጠበቅበት መሆኑን ይጠቁማሉ። በድርጅቱ ውስጥ ያሉት ሽማግሌዎች የጉልበት ሥራ የማይሳተፉ መሆኑን፤ ሆኖም በበሩ ዙሪያ ያለው ሥራ ብልሃትና ልምድ የማይጠይቅ ስለሆነ ያንን የሚሠሩት ሽማግሌዎች መሆናቸውን ያስረዳሉ። ከዚህም ሌላ ሽማግሌዎች የማስተባበር፣ የማስማማት፤ የመምከር ኃላፊነት ያላቸው በመሆኑ ለቤት ሥራው ስኬት የሚጫወቱት ሚና ቀላል አለመሆኑን አስገንዝበዋል።

እንደ አቶ ከቤታና ገለፃ፤ በሲዳማ ባህል መሠረት ሽማግሌዎች ትልቅ ክብርና ተሰሚነት ስለአላቸው ‹‹ለሙርቻ›› (መሪዎች) ጭምር የሥራ አመራር ስልትና ምክር ይሰጣሉ። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ሽማግሌዎች ‹‹ጭሜሳ›› የሚባሉ በዕድሜ ወይም በ‹‹ሉዋ›› ታላቅ የሆኑ ሰዎች ናቸው። ‹‹ሙርቻ›› ግን የሥራ ችሎታና ጠባዩን አይተው አባላት የሚመርጡት ሰው ነው።አንድ ቤት ሠርቶ ለመጨረስ ከሦስት ሳምንት እስከ ሁለት ወር ይወሰዳል። በዚህ ረዥም ጊዜ ውስጥ ምግብና ቡና ለሠራተኞቹ የሚያቀርበው ባለቤቱ ራሱ ነው።ሆኖም ጓደኞቹ ይረዱታል።በተለይም የሚስቱ ጓደኞች የሆኑ ሴቶች በዚህ ዕለት ‹‹እኔ ስለምረዳሽ ምግብ አታሰናጂ›› ብለዋት ለሴትየዋ ይነግሯታል። በተባለው ቀን እነርሱ ያቀርባሉ። በዚህ ዓይነት የሚቀርበው ምግብ ‹‹ካአጡ›› ይባላል። እንዲህ ላደረጉ ሰዎች (ሴቶች) ቤት በሚሠራበት ጊዜ ውለታ ይመለስላቸዋል። ቤት ተሠርቶ በሚያልቅበት ጊዜ ከብት ታርዶ ግብዣ ይደረጋል፡፡

ስለሆነም ወንዶቹ የቤቱን ሥራ በሚጀምሩበት ጊዜ ሴቶቹ ደግሞ በበኩላቸው ሴቷን ለመርዳት በአንድ ላይ ተሰባስበው ምግብ ማዘጋጀት ይጀምራሉ።የአካባቢው ዋና ምግብ የሆነውና ከእንሰት የሚሰራው ‹‹‹ዋሳ›› (ቆጮ) ብዙ ሥራ የሚጠይቅ በመሆኑ ሴቶች በተቻላቸው መጠን ሥራውን ቀደም ብለው ይጀምራሉ።አሮጊቶቹም በቦታው ተገኝተው ቀለል ያለ ሥራ የሚያከናውኑ መሆኑን ጠቅሰው፤ ሆኖም የአሮጊቶቹ ሥራ ከሽማ ግሌዎቹ ጋር ሲነፃፀር የሽማግሌዎቹ ከባድ ነው። ይሁንና በሲዳማ ማህበረሰብ ከወንዶቹ መካከል ሽማግሌዎች እንደሚከበሩ ሁሉ ከሴቶች በኩልም አሮጊቶቹ የሚከበሩ ናቸው። በሲዳምኛ ቋንቋ ሽማግሌዎች ‹‹ጭሜሳ›› አሮጊቶቹ ደግሞ ‹‹ቃርቾ›› የሚል መጠሪያ አላቸው።

‹‹ቤት በሚሠራበት ጊዜ ሴቶቹ ‹‹ሐኖ›› የተባለውን ዘፈን ይዘፍናሉ። ወንዶቹ ደግሞ ‹‹ዌዶ›› የተባለውን ጨዋታ ይጫወታሉ››። ቤቱ ተሠርቶ ሲያልቅ ደግሞ ትልቅ ግብዣ የሚደረግ ሲሆን፤ የዚያኑ ዕለት ማታ ወጣቶቹ ተሰብስበው ‹‹ፉኖ›› የተባለውን ዘፈን እየዘፈኑ ሌሊቱን በሙሉ ያነጋሉ።ለግብዣው ከታረደው ሥጋ መካከል ወርችና ጎድን (ሃዬና ሜጣቄ) ለሴቶች የሚሰጥ ሲሆን፤ የቤቱ ሥራ ከተፈፀመ በኋላ የሚደረገው ግብዣ ደግሞ ‹‹ኢማኔ›› እየተባለ ይጠራል።ቤት ሥራ ለመጀመር ማለትም መሠረት (ጋታ) ለመጣልም ሆነ ‹‹ኢማኔ›› (የቤት ምርቃት) ለማድረግ ወደ ከዋክብት ቆጣሪዎች ዘንድ በመሄድ መልካም ቀን ይመረጣል፤ ‹‹አያንቶ›› በሚነግሩት ቀን ድርጊቱ የሚፈፀም ይሆናል።

**ኦሳ**

እንደ አቶ ከቤታና ገለጻ፤ ከሦስት እስከ ሰባት ያሉ ጭናንቾች (ጎጦች) በመሰብሰብ አላ የተባለውን ድርጅት ያቋቁማሉ። ለዚህ ድርጅትም ሙርቻዎች ይኖሩታል። የአመራረጡ ሁኔታ ከጭናንቶች ጋር አንድ ነው። ዋናውና ምክትል (ላይንክ) ‹‹ሙርቻ›› የሚመረጡት በመላው ‹‹አላ›› ሲሆን ለየ‹‹ጭኛኝቶች››ም አንድ ተጠሪ ይኖራል። የዚህ ድርጅት ዋና አገልግሎት ለቀብር ለለቅሶ፣ ጥል በማስወገድ ሰላም መፍጠር፣ መስዋት ማቅረብ፤ ሸንጎ መሰብሰብ እና የመሳሰሉት ናቸው። አላም ለአባላት ቤት ይሠራል። ሆኖም ለግብዣ ብዙ ወጪ ስለሚጠይቅ በአላ ቤት ለመሥራት የሚደፍሩ ሰዎች በጣም ጥቂት (ሀብታሞች) ናቸው። አንድ ሰው ከፍተኛ ጉዳት ቢኖረውም አላ እንዲሰበሰብለት ለሙርቻ (መሪዎች) ሄዶ ይነግራል። ሙርቻም ለየጭናንቾ ተጠሪዎች ይነግራል። ተጠሪዎቹም ለየአባላቱ ትዕዛዝ ያስተላልፋሉ፤ አባሎቹም በተባለው ቀንና ሰዓት ወደተጠሩበት ቦታ በመሄድ የተነገራቸውን ጉዳይ ያከናውናሉ።በ ‹‹አላ›› ውስጥ ያለው ድርጅታዊም ሆነ አስተዳደራዊ ሁኔታ ከጭናንቾ ጋር አንድ ዓይነት ነው።

ቤት ለመሥራት ሕዝብ የሚገለገልባቸው ዕቃዎች በአካባቢው ከሚገኙ ሀብቶች (ደን) መሆኑን ጸሐፊው ያመለክታሉ። በዚህ መሠረት የደጋው ቤት የሚሠራው በአካባቢው ከሚገኙ እንጨቶች መሆኑን ጠቅሰው፤ በመሆኑም ቤት ለመሥራት የሚያስፈልጉ ዕቃዎች በመጀመሪያ ከተሰበሰቡ በኋላ ጥሩ ቀን ከ‹‹አያንቶ›› (ኮከብ ቆጣሪዎች ወይም ቀን ተንባዮች) የሚጠየቁበት ሂደት መኖሩን ጸሐፊው ያብራራሉ። ‹‹በዚያች ‹‹አያንቶ›› በሚነግሩት ቀን ቤት የሚሠሩ ሰዎች በቦታው ይገኛሉ፤ ሰውዬው አካባቢውን ከአሳየ በኋላ ትክክለኛ ቦታ (ሳይት) በሰዎቹ ይመረጣል›› ይላሉ። የቤቱን መሠረት የሚጥለው ባለቤቱ ወይንም የአካባቢው ‹‹ጭሜሳ›› ሊሆን እንደሚችልና ከዚያም በተመረጠው ሥፍራ በመሀከሉ ላይ አንድ ‹‹ሂልቾ›› ቀጭን አጠና ወይንም ዱላ የሚተከል መሆኑን ያስረዳሉ።

እንደእርሳቸው ማብራሪያ፤ ቤቱ ሲሠራ ‹‹ሂሊቾ›› (ምሰሶ) የሚቆምበት ሲሆን በዚህ ዱላ ላይ በክንድ (ጭጊሌ) ወይንም በጫማ ‹‹ሃርኡማ›› የተለካ ‹‹ጡሾ›› (ገመድ) ያስሩና ርቀቱ በርሱ እየተለካ ዙሪያው ‹‹ጋታ›› ይቆፈራል። በዚህ ዓይነት መሠረት ሲቆፈር፣ ከምሰሶ እስከ ግድግዳ ያለው ርቀት ሲለካ በሁሉም አቅጣጫ እኩል ይሆናል። ስለሆነም ቤቱ ሲሠራ ፍጹም የሆነ ክብ ቅርጽ ይኖረዋል። በዚህ ዓይነት መሠረቱ ከተቆፈረ በኋላ ቁመታቸው እኩል የሆነ ጠርብ ‹‹ጣራ›› ወይንም ‹‹ኩሩሜ›› የሚባል ይተካል። ይህም እንዳይናጋ በትክክል ተይዘው አፈር ይመለሳል። ከዚያም ቀደም ባለጊዜ በሌላ ቦታ ተሠርቶ የቆየውን ለወደፊት የቤቱ ጣሪያ የሚሆነውን ‹‹ቃልቾ›› (ጣሪያው ላይ የሚታሰር ርብራብ) ያመጡና በቤቱ መሃል ያኖሩታል። በ‹‹ቃልቾ›› መሀል ወይም ጫፍ ላይ ጠባብ የሆነ ቀዳዳ አለው። በዚህ ቀዳዳ ነው ቤቱ ተሠርቶ ሲያልቅ የሚገባው የምሰሶው ጫፍ ብቅ የሚለው፡፡

‹‹እንግዲህ በተተከለው ጠርብ ላይ ተደርበው ‹‹ሕሎ›› የተባሉት ቀጫጭን አጠናዎች ይተከላሉ።አሁን በግድግዳው ላይ ከውስጥና ከውጭ አጠናዎችን እያጋደሙ ሁለት ጠንካራ ‹‹ዳጋሌ›› ማገር ይሠራል።ማገሩ የሚታሰረው በጣም ጠንካራ በሆነ ‹‹ዲኪቻ›› በሚባለው ሐረግ ነው›› ይላሉ። ይህም ተሠርቶ ካለቀ በኋላ በመሀል ላይ ያለው ‹‹ቃልቾ›› በጊዜያዊ ምሰሶ ላይ የሚሰቀል መሆኑና በመቀጠልም በቃልቾው ላይ ያለው ‹‹ሄርቾ›› (ጣሪያው ላይ የሚታሰር እንጨት) ላይ እየቀጣጠሉ ተብትበው የሚሠሩበት ሂደት መኖሩን ነው ያስገነዘቡት፡፡

ስለዚህ ከላይ የተሰቀለው ቃልቾ በዚህ ዓይነት ወደታች እያደገ ይመጣና ከጠርቡ ጋር ከተተከለው ሕሎ (አጠናዎች) ጋር የማገናኘት ሥራ እንደሚሠራ አቶ ከቤታና ጠቁመው፤ እነዚህ አጠናዎች እየተሳቡ ከላይ ከመጣው ‹‹ሄርቾ›› ጋር በማሰር ቤቱ በጣም እንዲወጠር የሚደረግ መሆኑን ያስረዳሉ። በዚህ ዓይነት ተሠርቶ ሲጠናቀቅ እንደ አካባቢው ሁኔታ ማለትም ደጋ ከሆነ በሆንጮ (የቀርካሃ አቃፊ) በሌላ አካባቢ ከሆነ ግን ደግሞ በ‹‹ቡዮ›› ለቤት ኪዳን ተብሎ የሚያድግና ከሌላው ለየት ያለ ሣር የሚከደንበት የአሠራር ሂደት መኖሩን ያብራራሉ። በመጨረሻም ቤቱ ተሠርቶ ሲጠናቀቅ ግለሰቡ ከ‹‹አያንቶ›› ጥሩ ቀን ጠይቆ ወደ ቤቱ የሚገባ መሆኑን ነው የጠቆሙት፡፡

እንደፀሐፊው ማብራሪያ፤ ቤቱ ‹‹አልእዶ›› እና ‹‹ሃድሮ›› ተብሎ ለሁለት ይከፈላል። አልእዶ የሰው መኖሪያ ሲሆን በስፋት ከ‹‹ሃድሮ›› ይበልጣል። ‹‹ሃድሮ›› ወይም ጋጣ የከብት መኖሪያ ይሆናል።‹‹አልእዶ›› እንዲሁም ‹‹ዱኡኮ›› (መጋረጃ) በመባል የሚታወቀው ግድግዳ ለሁለት ይከፈላል። ይህ ግድግዳ በደጋው አካባቢ ቀጭን ሆነው በተሰነጠቀና ጥልፍ በሚመስል ቀርከሃ ስለሚሠራ በጣም ያምራል። በሌላው አካባቢ ግን በአካባቢው በሚገኝ እንጨት ይሠራል።ሆኖም ሀብታሞቹ ከደጋ ቀርከሃ አስመጥተው ነው የሚሠሩት። ምክንያቱም የደጋው ቀርከሃ የተሠራው ትልቅ ክብር የሚሰጠው በመሆኑ ነው። የባልና የሚስት መኝታ እዚያው ውስጥ ይሆናል።በአካባቢው ማህበረሰብ ‹‹ቦሣሎ›› (ሳሎን) እየተባለ የሚጠራው ክፍል ደግሞ የልጆች መኖሪያ ሲሆን፣ ቀላል ዕቃዎችና የምርት መሣሪያዎች ይቀመጣሉ።እንግዳ ሲመጣም ጊዜያዊ መኝታ ተዘጋጅቶለት በዚህ ክፍል ያድራል።

ጸሐፊው ርዕሰ ጉዳያቸውን ሲደመድሙም የሲዳማ ሕዝብ ካሉት ጥንታዊ እሴቶች መካከል ይህ ቤትን በደቦ የመሥራት ባህል ዋነኛው መሆኑን፤ ለዘመናትም ከትውልድ ትውልድ በመሻገር ለማህበረሰቡ ከፍተኛ ጠቀሜታ ሲያበረክት መቆየቱን አስገንዝበዋል። በተለይም በደቦ በመሥራት ሂደት የሕዝቡን ማህበራዊ ትስስር ከማጠናከሩም ባሻገር አቅም የሌላቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎች በማገዝ ከስጋትና ችግር በመገላገል ረገድ አወንታዊ ሚና ሲጫወት መቆየቱን አስረድተዋል።ይህ ከፍተኛ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ያለው እሴት ታዲያ አሁን አሁን በተወሰነ ደረጃ እየተሸረሸረ መምጣቱን የአካባቢው ተወላጆች ይናገራሉ። በተለይም ባህላዊ የቤት አሠራር ወደ ዘመናዊ (ቆርቆሮ) ቤት አሠራር እየተተካ በመምጣቱ ሁሉም በተናጠል ቤቱን ከፍሎ እንደሚያሠራ ይጠቁማሉ። ይህ ደግሞ ባህላዊውን ዘዴ እንዲረሳ ከማድረጉም ባሻገር አቅምንም የሚፈታተን፤ ወጪንም የሚጨምር መሆኑን ያስረዳሉ። ከሁሉ በላይ የመረዳዳትና በጋራ ተሳስቦ የመኖር ባህሉን እየሸረሸረ በመሆኑ የሚመለከታቸው አካላት ለዚህ መልካም እሴት ዳግም ማበብ የበኩላቸውን ርብርብ ማድረግ ይገባቸዋል።

ማህበራዊ

# ወጣቶች

# በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ

አስናቀ ፀጋዬ

ወጣት ተስፋ ወንድሙ ከሁለት አመት ከስድስት ወር በፊት በአክሱም ዩኒቨርሲቲ የሜካኒካል ኢንጂነሪንግ ተማሪ ነበር። ሆኖም በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል በተቀሰቀሰው ጦርነት ምክንያት ትምህርቱን አቋርጦ ወደ አዲስ አበባ ለመመለስ ተገዷል። ትምህርቱን አቋርጦ ወደ አዲስ አበባ ከተመለሰ በኋላም ከትምህርት ባለፈ በርካታ ነገሮችን የመሞከር ፍላጎት ነበረው።

በርግጥ ታላላቅ ወንድሞቹና እህቶቹ በትምህርታቸው ጫፍ የደረሱ በመሆናቸው የእርሱም ዕጣ ፈንታ በትምህርቱ መግፋት እንደሆነ ቢረዳም በቢዝነሱ ዓለም ስኬታማ ለመሆን አጥብቆ ይመኝ ነበር።ለዚህም ሰዎች በቢዝነስ ዓለም እንዴት ስኬታማ መሆን እንደቻሉና ቢዝነስ በራሱ ምን እንደሆነ ለማወቅ ዩቲዩብ ይመለከታል፤ መረጃዎችን ያያል፤ ያገላብጣል፤ይመራመራል። ራሱን ወደ ቢዝነሱ ዓለም የማንደርደር ሃሳብ ውስጥ እያለ ግን አንድ የስልክ ጥሪ ከጓደኛው ደረሰው።

ጓደኛው ሱራፌል ይባላል። የአክሱም ዩኒቨርሲቲ ጓደኛው ነው።በግል ስብእና ግንባታና አመለካከት ለውጥ ዙሪያ ስልጠናዎችን በመውሰድ ራስን ማብቃት እንደሚቻል መረጃ ሰጠው።አላቅማማም። ስልጠናው ወደሚሰጥበት ቦታ ወዲያው አመራ። የሚጠበቅበትን ክፍያ ከፈፀመ በኋላ ስልጠናውን መከታተል ጀመረ። ራስን ስለማበልፀግና የአመለካከት ለውጥ ማምጣት ላይ ያተኮሩ ስልጠናዎችን ለሦስት ወራት ያህል ተከታትሎ አጠናቀቀ።

በዚህም የራሱን ራዕይ ማወቅ ቻለ። ስለ ሕይወቱና ወደዚህ ምድር የመጣበትን ምክንያትም ለመረዳት ችሏል። በተለይ ደግሞ ሲያስባቸው የነበሩና ሊሳኩ አይችሉም ያላቸውን ትላልቅ ህልሞችን ይቻላል በሚል መንፈስ ድጋሚ አድሷቸዋል። ከምንም በላይ ደግሞ ለነገሮች ቸልተኛ የሚባል ሰው የነበረ እንደመሆኑ ስልጠናውን ከተከታተለ በኋላ ይህን ባህሪውን ቀይሯል።

በአሁኑ ጊዜ በዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ አንደኛ አመት የማርኬቲንግ ማኔጅመንት ትምህርቱን እየተከታተለ የሚገኘው ወጣት ተስፋ ስልጠናዎችን ለሌሎች ወጣቶች በማካፈልና በማስተዋወቅ ገቢ እያገኘ ነው። እስካሁን ባለው ሂደትም ሰባት ለሚሆኑ ጓደኞቹና ቤተሰቦቹ ስልጠናውን እንዲወስዱ ማድረግ ችሏል። በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ እንዲሉም ስለዚህም ወጣት ተስፋ ገቢ እያገኘም፤ የወጣቶችን አመለካከት እየገነባም ሕይወቱን በመምራት ላይ ይገኛል፡፡

ወጣት ተስፋ ስልጠናዎች ለሌሎች በማካፈልና ስልጠናውን እንዲወስዱ በማድረግ ብሎም ኩባንያውን በማስተዋወቅ ሥራ እስካሁን ባለው ሂደት በመጀመሪያው አንድ አመት ሥራው 200 ሺ ብር ገቢ አግኝቷል። እስካሁን ባለው ሂደትም ባጠቃላይ 2 ነጥብ 5 ሚሊዮን ብር ማግኘት ችሏል። በወር ደግሞ ከ150 እስከ 250 ሺ ብር ያገኛል።

ወጣት ተስፋ የወጣቶችን ስብና በመገንባት ውጤት የኩባንያውን ገፅታ ከገነቡና ከኩባንያው ጋር በመሥራት ውጤት ካስመዘገቡ ወጣቶች መካከል አንዱ በመሆኑ የአፍሪካዊቷ ሲሸልስ ደሴት የደርሶ መልስ ጉብኝት ተጠቃሚ ለመሆን በቅቷል። ወጣቶች ሸቀጥን ብቻ ሳይሆን ሃሳብንም በመሸጥ ከራሳቸው አልፈው ለአገር የሚተርፍ ገቢ ማግኘት እንደሚችሉ ወጣቱ ምክሩን ይለግሳል።

በርግጥ ሥራው በርካታ ውጣውረድ ያለበትና ልፋትን የሚጠይቅ ቢሆንም በትጋትና በብልሃት ከተሠራበት ጥሩ ገቢ የሚገኝበት መሆኑን ይናገራል ወጣት ተስፋ። አሁን ላይ በወር የሚያገኘው ገቢ ቀደም ሲል በአመት የሚያገኘው እንደነበረና ነገር ግን አሁን ላይ ጠንክሮ በመሥራቱ ወርሃዊ ገቢውን ማሻሻል እንደቻለም ነው የሚናገረው። በቀጣይ ደግሞ ዓለም አቀፍ አነቃቂ አሰልጣኝ በመሆን ከሦስት እስከ አምስት ባሉት አመታት ውስጥ ከ30 እስከ 50 ሺ የሚጠጉ ሰዎችን የማሰልጠን ህልም አለው።

ሌሎች ወጣቶችም በቅድሚያ ራዕይ ሊኖራቸው እንደሚገባ ይገልፃል። በመቀጠል ደግሞ ህልም ሊኖራቸው እንደሚገባና ያላቸውን ህልም እውን ማድረግ እንደሚችሉ ማመን ይኖርባቸዋል ይላል። ለህልማቸው እምነት ካላቸው ሁሉንም ነገር ማሳካት እንደሚችሉም ይጠቁማል።

ወጣት ነፃነት ዘነበ በወጣቶች ስብዕና ዙርያ የሚሠራ ድርጅት የቦርድ ሰብሳቢ ነው።እርሱ እንደሚለው ማህበሩ ከተቋቋመ ሦስት አመት ሞልቶታል። ከ300 በላይ የአክሲዮን ባለድርሻዎችንም አፍርቷል። በነዚሁ ሦስት አመታት ውስጥ ለወጣቶች በገፅ ለገፅና በበይነ መረብ የተለያዩ በግለሰብ ስብእና ግንባታ ላይ ያተኮሩ ስልጠናዎችን ለወጣቶች በመስጠትና በማብቃት ከኩባንያው ጋር አብረው በመሥራትና የራሳቸውን ሥራ በመፍጠር ተጠቃሚ እንዲሆኑ አድርጓል።

እንደ ቦርድ ሰብሳቢው ገለፃ ማህበሩ በዋናነት ደስተኛ፣ ስኬታማና ለሕይወት መሠረት የሚጥሉ አምስት የስልጠና ጥቅሎችን ያቀርባል። እነዚህ የስልጠና ጥቅሎች በሂፕኖ ቴራፒ፣ ኒዩሮ ሊንጉስቲክ ፕሮግራሚንግና ሱዶ ሳይንሶች ላይ መሠረት ያደረጉ ናቸው።እስካሁን ባለው ሂደትም ከ21 ሺ በላይ የሚበልጡ ወጣቶችን በማሰልጠን ዓላማ ያላቸው፣ ዋጋቸውን የሚያውቁ፣ ከደባል ሱስ የፀዱ፣ ለአገር ሰላም የቆሙ፣ ሥራ ፈጠራ ላይ ያተኮሩ ወጣቶችን ለማፍራት ችሏል።

በዚሁ የገፅ ለገፅና በይነ መረብ ስልጠና አማካኝነት ባለራእይና ቀና አስተሳሰብን በወጣቶች ውስጥ አስርጿል። ሰልጣኞችም የራሳቸውን ሥራ እንዲፈጥሩ አስችሏል፤ እያስቻለም ይገኛል። በበይነ መረብ በርግጥም ስልጠና ይገኛል የሚለውን በብዙዎች ዘንድ ያለውን ጥርጣሬ ቢኖርም ምንያህል የገበያው ፍላጎት እንዳለ ኩባንያው ማየት ተችሏል።

በዋናነት ኩባንያው ስልጠናዎቹን የሚያቀርበው በአካል ብቻ ሳይሆን በኢ- ለርኒንግ ጭምር በአማርኛ፣ በኦሮሚኛ፣ በእንግሊዝኛና፣ በትግርኛ ቋንቋዎች በመሆኑ ልዩ ያደርገዋል። ይህም ሰዎች በተለይ ደግሞ ወጣቶች ከቤታቸው፤ ከኢትዮጵያ ውጪም ሆነው በቨርችዋል መማሪያ ክፍሎች ውስጥ እየገቡ ስልጠናዎችን በተመቻቸው ሰዓት በቀላሉ መሳተፍ ይችላሉ።

የኩባንያው ዋነኛ አላማም ባለራእይ፣ ቅን፣ ጤናማና ባለፀጋ ትውልድ ማፍራት እንደመሆኑ ይህንኑ ዓላማ ለማሳካት አገር ማለት መሬት ሲደመር ሰው ነው ሰው ደግሞ የሚስለው አስተሳሰቡን በመሆኑ አስተሳሰብም የሚቀረፅና የሚገራ ነው ብሎ ያምናል።ሰው ድሃም ሀብታምም ሆኖ አልተፈጠረም፤ ክፉም ደግም ሆኖ አልተፈጠረም፤ ለዚህም በአገሪቱ ውስጥ ያሉ መድረኮች፣ በቤተሰብና በግል ያለ አስተሳሰብ ትልቅ አስተዋፅኦ አለው ብሎ ኩባንያው ያስባል።

ጥሬ ዕቃዎችን ብቻ ሳይሆን ስልጠናዎችንም ጭምር ወደ ውጭ አገራት በመላክ ገቢ ማግኘት ይቻላል።የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክም የውጭ ምንዛሬ አካውንት ከፍቶ በውጭ አገራት ያሉ ሰዎች በውጭ ምንዛሬ ስልጠናዎችን እየገዙ የውጭ ምንዛሬ ለአገሪቱ ማመንጨት እንዲችሉ ሁኔታዎች ተመቻችተዋል። በመጪዎቹ ስድስት ወራት ደግሞ በደቡብ ሱዳን፣ ኬንያ እና እሥራኤል ቅርንጫፎችን ከፍቶ በሞያቸውና በትምህርት ደረጃቸው ላቀ ያለ ደረጃ ላይ ላሉት ዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠርና የሚጠበቅበትን ግብር ለመንግሥት በማስገባት ለአገሪቱ በየወሩ ከግማሽ ሚሊዮን ብር በላይ የውጭ ምንዛሬ ለማስገባት እየሠራ ይገኛል።

ኩባንያው ስልጠናዎችን በአምስት ጥቅሎች ለወጣቶች ሲሰጥ በትንሹ ከ3000 ብር አንስቶ እስከ ትልቁ 50 ሺ ብር ድረስ ይጠይቃል። ስልጠናውን ለመስጠት ዝቅተኛው ሦስት ሳምንት፤ ከፍተኛው ደግሞ ስድስት ወር ይፈጃል። ስልጠናዎቹም አነቃቂ አይደሉም። ይልቁንም ወጣቶች ስልጠናውን ወስደው የራሳቸውን ሥራ ፈጥረው እንዲሠሩ ያስችላል።በሌላ በኩል ደግሞ ምንም ገቢ የለኝም ለሚሉ ወጣቶች ከኩባንያው ጋር በጋራ ሆነው በመሥራት በተለይ ደግሞ የሚሰጣቸውን ስልጠናዎችን ለሌሎች በማካፈልና በማስተዋወቅ ከሚገኘው ሽያጭ የኮሚሽን ክፍያ ማግኘት ይችላሉ።

የኩባንያው አሰልጣኞች በወር ለሦስት ቀናት በተለያዩ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ውስጥ በመገኘት ስልጠናዎቹን በነፃ የሚሰጡበትን አሠራር ዘርግቷል። በተለይ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በሚገኙ ከ13 በላይ በሚሆኑ ዞኖች ውስጥ ስልጠናዎችን ሰጥቷል።በመንግሥት መስሪያ ቤቶችም በኩል ለሴት ፓርላማ የካውከስ ተጠሪዎች በመጪዎቹ ሁለት አመት በነፃ ለማሰልጠን እቅድ ይዞ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። የመጀመሪያውን ጥቅል ስልጠናም ከሦስት ወር በፊት ሰጥቷቸዋል።

ወጣት ነፃነት እንደሚለው ኩባንያው ከሚያቀርባቸው ስልጠናዎች 60 ከመቶ የሚሆነውን ገቢውን ማለትም ከ1 ሺ ብር ላይ 600 ውን እያሰላ ከገፅታ ገንቢ ወጣቶች ጋር አብሮ በመስራትና አብረውት ሰልጥነው በስልጠናው ደስተኛ ለሆኑ ወጣቶች ኮሚሽን ይከፍላል። እስካሁንም እየከፈለ ይገኛል።በዚሁ አሠራር መሠረት ኩባንያው በሦስት አመታት ውስጥ ከ101 ሚሊዮን ብር በላይ ኮሚሽን ለገፅታ ገንቢዎች ከፍሏል።

እነዚህ ገፅታ ገንቢዎች ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት ጀምሮ ያሉ፣ ከኮሌጅና ዩኒቨርሲቲ ተመርቀው ያለሥራ የተቀመጡ፣ በተለያዩ ሱስ ውስጥ ተዘፍቀው የነበሩ ወጣቶች ናቸው። ወጣቶቹ በኩባንያው የሚሰጡ በግል ስብእና ግንባታ ዙሪያ ያተኮሩ ስልጠናዎችን ተከታትለው ከኩባንያው ጋር በመሥራት ዛሬ ላይ የስልጠናዎቹን ጠቀሜታ ሌሎች በማካፈልና ወደኩባንያው እንዲመጡና እንዲሰለጥኑ በማድረግ የኩባንያውን ገፅታ ገንብተው በወር ከ50 እስከ 60 ሺ ብር ገቢ በማግኘት ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን መደገፍ ችለዋል።

ኩባንያው በአሁኑ ወቅት በአዲስ አበባና በአዳማ ከተማ ካሉት ቅርንጫፎች በተጨማሪ በመጪዎቹ አምስት አመታት የቅርንጫፍ ስልጠና ማዕከላቱን በመላው አገሪቱ የማስፋፋት እቅድ አለው። የሚሰጣቸውን ስልጠናዎች ከአገር ውስጥ በተጨማሪ ወደተለያዩ የውጭ አገራት ተደራሽ በማድረግና በውጭ አገር የሚሸጠውን ስልጠና በውጭ ምንዛሬ ወደ አገር ውስጥ የማስገባት እቅድም ነድፏል።ከ300 ሺ በላይ ወጣቶችን በማሰልጠን ከፍተኛ ግብር በመክፈል ከ10 ሺ በላይ ገፅታ ገንቢዎችን በየሳምንቱ ኮሚሽን ለመክፈል የሚያስችል አቅም ላይ የመድረስ ውጥንም ይዟል። ከዚህ ባለፈ ኩባንያው በትራንስፖርት አገልግሎት ዘርፍ ላይም የመሳተፍ ሃሳብ አለው።

በኢትዮጵያ በየአመቱ በርካታ ወጣቶች በልዩ ልዩ የትምህርት መስኮች ተመርቀው ይወጣሉ።የአብዛኛዎቹ ወጣቶች ፍላጎትም በተማሩበት የትምህርት መስክ ተቀጥሮ መሥራት ነው።ይሁንና በመንግሥትም ሆነ በግል ተቋማት የሚወጡ የሥራ ቅጥር መደቦች ውስንና ከተመራቂው ወጣት ቁጥር ጋር ተመጣጣኝ አይደሉም።ይህንኑ ተከትሎም አብዛኛው ተመራቂ ወጣት ያለ ሥራ ለመቀመጥ ይገደዳል።

ሆኖም እጅን አጣጥፎ ያለ ሥራ ከመቀመጥ ሌሎች አማራጮችን ማማተሩ ከሁሉም ወጣት ይጠበቃል።በተለይ ደግሞ የተዛባ አመለካከትን በማስወገድና የራስን የግል ስብእናን በስልጠና በማዳበር በልዩ ልዩ መስኩ በጋራና በተናጠል ሥራ በመፍጠር ራስንና ቤተሰብን መለወጥ እንደሚቻል ተገንዝበው ዛሬ ነገ ሳይሉ ግራ ቀኝ አይተው ለለውጥ ሊነሱ ይገባል። ሰላም!

> **ጥሬ ዕቃዎችን ብቻ ሳይሆን ስልጠናዎችንም ጭምር ወደ ውጭ አገራት በመላክ ገቢ ማግኘት ይቻላል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክም የውጭ ምንዛሬ አካውንት ከፍቶ በውጭ አገራት ያሉ ሰዎች በውጭ ምንዛሬ ስልጠናዎችን እየገዙ የውጭ ምንዛሬ ለአገሪቱ ማመንጨት እንዲችሉ ሁኔታዎች ተመቻችተዋል**

# የምድር በረከት

# የማዕድን ግብዓት ተጠቃሚ አምራች ኢንዱስትሪዎችን አቅም የመገንባት የጋራ ጥረት

ስምስም መንግሥቱ

በሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያው የአስር ዓመት መሪ እቅድ ለሀገራዊ ምጣኔ ሀብት እድገት ወሳኝ ተብለው ከተመረጡ አምስት ዘርፎች መካከል ማዕድን አንዱ መሆኑ ይታወቃል። ዘርፉን የሚመራው የማዕድን ሚኒስቴርም በማዕድን ጥናት፣ ልማትና ግብይት ላይ የሚካሄዱ ተግባሮችን በመምራትና በመከታተል የሚጠበቅበትን ለመወጣት ጥረት እያደረገ ይገኛል።

ሚኒስቴሩ ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚያስችለውን አደረጃጀት በመከተል (ሪፎርም በማድረግ) በሥሩ ተጠሪ የሆነ የማዕድን ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩትን አቋቋሟል። የዚህ ኢንስቲትዩት ዋና ተልዕኮና ተግባር ማዕድን የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎችን መደገፍ ነው። ድጋፉም ከጥሬ እቃ ግብዓት ፍለጋ ጀምሮ ጥራትን እስከ ማረጋገጥ ፣ የሀብት መጠንን እስከ መለየት፣ በአጠቃላይ ከግብዓት እስከ ምርት ሂደት ድረስ የሚዘልቅ ይሆናል። በተጨማሪም በቴክኖሎጂና በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል በማፍራት ላይ ሙያዊ እገዛ በማድረግ እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ለዘርፉ የፖሊሲና ስትራቴጂ ሰነድ በማዘጋጀትም ድጋፍ ያደርጋል።

የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ጉታ ለገሠ እንደሚናገሩት፤ኢንስቲትዩቱ ኢንዱስትሪዎች የግብዓት አቅርቦት ችግር ሲያጋጥማቸው ችግሮቹ የሚፈቱባቸውን አማራጮችንም በጥናት ያመቻቻል። ለአብነትም እንደ ሀገር የብረት ግብዓት ችግር በማጋጠሙ ለተለያየ ጥቅም ውለው ከአገልግሎት ውጪ የተደረጉ የብረታብረት ቁርጥራጮች ለብረታ ብረት ኢንዱስትሪዎች ግብዓትነት እንዲውሉ በማመቻቸት ኢንስቲትዩቱ ተልዕኮውን ተወጥቷል። በሌሎችም ዘርፎች ክፍተቶች ሲፈጠሩ በጥናት የታገዘ የመፍትሔ አቅጣጫ በማዘጋጀት ለውሳኔ ያቀርባል። ሚኒስቴሩ የቴክኒክ ክንፍ በመሆን የማዕድን ዘርፍን እያገዘ ይገኛል።

ኢንስቲትዩቱ በዚህ ወቅትም በማዳበሪያ፣ በብረትና ማርብል ፕሮጀክት ቀርጾ በትኩረት እየሠራ ነው። ከዚህ በተጨማሪም በጌጣጌጥ ማዕድናት (ጄም ስቶን) ላይም ለውጦች እንዲመጡ ግፊት እያደረገ ይገኛል። የጌጣጌጥ ማዕድናት እሴት ተጨምሮባቸውና ሳይጨመርባቸው ለገበያ ቢቀርቡ የትኛው አዋጭ እንደሆነ ጥናት ተደርጓል።

የጥናት ግኝቱም እሴት ያልተጨመረበት ምርት ለገበያ ማቅረብ ዝቅተኛ ገቢ የሚያስገኝ መሆኑን ማመልከቱንና እሴት ያልተጨመረበት ሽያጭ መቆም እንዳለበትም ምክረ ሀሳብ የተቀመጠበት ጥናት እንደሆነ አስረድተዋል። ማዕድን ሚኒስቴርም ጥናቱን መሠረት አድርጎ የፖሊሲ ለውጥ እንዲያደርግ በኢንስቲትዩቱ በኩል ጥረት እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል።

ማዕድንን ተጠቅመው የሚሠሩ ኢንዱስትሪዎች ሥልጠና እንዲያገኙም እየተሠራ መሆኑንም ዶክተር ጉታ አመልክተዋል። ኢንስቲትዩቱ አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ለማዕድን ሚኒስቴር፣ ለኢንዱስትሪዎች፣ ለክልሎች፣ በማኅበር ተደራጅተው በማዕድን ዘርፉ ላይ ለሚሠሩ አካላት ድጋፍ ያደርጋል ብለዋል።

የማዕድን ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በ2014 በጀት ዓመት መቋቋሙን የጠቆሙት ዶክተር ጉታ፤ሙሉ ለሙሉ ወደ ሥራ የገባው ግን በተያዘው 2015 በጀት መሆኑን ተናግረዋል። በማዕድን ዘርፉ የተሻለ ውጤት ተመዝግቦ ለሀገር ምጣኔ ሀብት እድገት ከፍ ያለ አስተዋፅዖ እንዲኖረው የራሱን አሻራ ለማሳረፍ ጠንካራ እንቅስቃሴ እያደረገ መሆኑን አመልክተዋል።

ኢንስቲትዩቱ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት (ዩኒቨርስቲዎች) ጋርም በአጋርነት ይሠራል። ሰሞኑንም ከአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ጋር ለመሥራት የመግባቢያ ሰነድ ስምምነት ተፈራርሟል።



የማዕድን ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩትና የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሉጂ ዩኒበርስቲ በጋራ መሥራት የሚያስችሳቸውን የጋራ መግባቢያ ሰነድ ስምምነት በተፈራረሙበት ወቅት

በኢንስቲትዩቱና በዩኒቨርሲቲው መካከል ስለተደረገው ስምምነትና ከዩኒቨርስቲዎች ጋር ስላለው አጋርነት ዶክተር ጉታ እንዳብራሩት፤ ኢንስቲትዩቱ ከሚያከናውናቸው ተግባራት መካከል በተወሰኑት ላይ አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ ሚና አለው። ዩኒቨርስቲው ከቴክኖሎጂ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ የአምራቾችን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ በሚረዱ ሥራዎች ዙሪያ አደረጃጀት አለው። በዚህ ረገድ ጥሩ ድጋፍ ማድረግ ይችላል። ለመደገፍም ፍላጎት አለው። ለአብነትም በብረታብረት እንዲሁም በሀገር ውስጥ መለዋወጫ በማምረት አቅም ለመፍጠር የሚያስችል የተደራጀ ቤተሙከራ (ላቦራቶሪ) ባለቤት ነው። በመሆኑም ዩኒቨርሲቲው ያለውን የተደራጀ ቴክኖሎጂ ለማዕድን ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ያጋራል። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሥልጠናዎችንና የጥናት ሥራዎች በጋራና በተናጠል በመሥራት ሁለቱ አካላት ይደጋገፋሉ። ዩኒቨርሰቲው ያሰለጠናቸውን ተማሪዎች ለተግባር ልምምድ እንዲወጡ ሲያደርግም ኢንስቲትዩቱ ከአምራች ኢንዱስትሪዎች ጋር በማስተሳሰር ድጋፍ ያደርጋል።

ቴክኖሎጂ ተጠቅሞ ወጭ ቆጣቢ ምርት በማምረት ላይም በጋራ ይሠራሉ። ኢንስቲትዩቱ ካደረገው የቴክኖሎጂ ሙከራ መካከል አንዱ ከአፈር ያመረተው ለግንባታ የሚውል ብሎኬት ነው። ብሎኬቱ ኢንስቲትዩቱ ጥናት ካደረገ በኋላ የሠራው ሲሆን፣ የጥራት ደረጃውም በሚመለከተው የመንግሥት አካል ማረጋገጫ አግኝቷል። እንዲህ ያሉ የቴክኖሎጂ ሙከራ ምርቶች ወደ ተግባር ተለውጠው ጥቅም ላይ እንዲውሉ በኢንስቲትዩቱ በኩል ጥረት እየተደረገ ነው።

ከአፈር የሚሠራውን ብሎኬት ለመጭመቅ የሚያግዘውን ማሽን በሀገር ውስጥ መሥራት የሚቻልበት እድል መኖሩን የጠቆሙት ዶክተር ጉታ፤ የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ማሽኑን በመሥራት፣ በተለይ ደግሞ የተሻለ ቴክኖሎጂ በማፍለቅ ሊያግዝ እንደሚችል አመልክተዋል።

በፖሊሲና ስትራቴጂ ዝግጅት ዙሪያም ከዚህ ቀደም ዩኒቨርሲቲው ሥራዎችን መሥራቱን አስታውሰው፣ በፖሊሲና ስትራቴጂው ላይ የሚስተዋል ክፍተት ካለ እንደገና በመፈተሽ በቀጣይ 10 ዓመት ምን አይነት ፖሊሲና ስትራቴጂ እንደሚያስፈልግ አብሮ ለመሥራት መግባባት ላይ መድረሳቸውንና የመግባቢያ ሰነድ ስምምነት መፈራረማቸውንም አስረድተዋል። የመግባቢያ ሰነዱ በአጠቃላይ ቴክኖሎጂን በማላመድ፣ ለተለያየ ኢንዱስትሪ ግብዓት መሥሪያ ማሽኖች መለዋወጫ በሀገር ውስጥ መሥራት፣ የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ምርታማነት በመጨመርና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ በጋራ ለመሥራት ያስችላል ብለዋል። ሴሚናሮችና ወርክሾፖችን በጋራ ማዘጋጀትም ተጨማሪ የጋራ ተግባራት መሆናቸውን ጠቁመዋል።

በተቋማት መካከል ስለሚደረጉ ስምምነቶች ቀጣይነትና ውጤታማነት ዶክተር ጉታ ሲገልጹ «በኢንስቲትዩቱ የኃላፊ መቀያየር ቢያጋጥም ሥራው ቀጣይነት እንዲኖረው በሚያደርግ አደረጃጀት እንዲዋቀር ተደርጓል። አሁን እያከናወናቸው ያሉ ሥራዎች ቀጣይ እንዲሆኑ በኢንስቲትዩቱ ውስጥ አምስት የሥራ ክፍሎች ተዋቅረዋል። እነዚህ ተናብበው እንዲሠሩ በመደረጉ ሥራው ቀጣይነት ይኖረዋል» ይላሉ።

የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ምክትል ፕሬዚዳንት ዶክተር ዓለሙ ዲሣሣ እንደሚሉት፤ ዩኒቨርስቲዎች የመማር ማስተማር እና የምርምር ሥራ ተልዕኮዎች ያላቸው እንደመሆኑ አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ የተቀመጠውን ተልዕኮውን ለመወጣት ከተለያዩ ተቋማት ጋር በጋራ መሥራት ይጠበቅበታል።

«ከዩኒቨርስቲው ጋር የመግባቢያ ሰነዱን የፈረሙት የማዕድን ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት እና የኢትዮጵያ ጂኦሎጂ ኢንስቲትዩት ተግባር ተኮር ሥራዎችን ነው የሚያከናውኑት። ስለዚህ የዩኒቨርሲቲው ተመራማሪዎች ወይንም ምሁራን በተቋሙ ተገኝተው የሚያደርጉት ሙያዊ እገዛ እንዲሁም ተቋሙ ወደ ዩኒቨርስቲው በመሄድ የሚወስዳቸው አጫጭር ሥልጠናዎችም ሆኑ በሥርዓተ ትምህርት ተቀርጾ የሚሰጠው ትምህርት የተቋማቱንና የዩኒቨርስቲውን ጥረት ፍሬያማ ያደርጉታል። ሀገራዊ ለውጥም ያመጣል የሚል እምነት አለኝ» ሲሉ ዶክተር ዓለሙ ገልጸዋል።

በኢትዮጵያ ለአምራች ኢንዱስትሪው ግብዓት የሚውል የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሰፊ የማዕድን ሀብት መኖሩን መረጃዎች ያመለክታሉ። ሀብቱን ጥቅም ላይ ለማዋል ሙከራዎች ቢደረጉም የሚፈለገው ስኬት ላይ መድረስ ግን እንዳልተቻለ ይነገራል። በዚህ ረገድ በአንድ በኩል በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ልማቱ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ አለመሆኑና የትኩረት ማነስና የመሳሰሉት ጉዳዮች ይጠቀሳሉ።

ዶክተር ዓለሙ እንደሚያስረዱት፤ ለማዕድን ልማቱ ትልቁ ማነቆ የሆነው የቴክኖሎጂ እጥረት ነው። ቴክኖሎጂና የሰው ሀብት ልማቱ የተነጣጠለ አይደለም። በማዕድን ሀብት ፍለጋ ላይ በቂ የሆነ የሰው ኃይል ካለ ቴክኖሎጂን ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ቀላል እንደሆነ፣ ሁለቱ ከተሟላ በኋላ ደግሞ ቀጣይ የሚሆነው ሀብት የማሰባሰብ ሥራ ነው።

በቴክኖሎጂና በሰው ሀብት ልማት ላይ ቁልፍ የሆነ ሥራ መሠራት እንዳለበትም ፣ዶክተር ዓለሙ ተናግረው፣ ይህም ከዘርፉ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ለማግኘት፣ እንደ ሀገር የተያዘው አቅጣጫ ውጤታማ እንዲሆን የሚያስችል መሆኑንም አመልክተዋል።

ዩኒቨርሲቲዎች በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል እያፈሩ ቢሆኑም ተማሪዎቻቸውን በተግባር በተደገፈ ትምህርት ባለማነጻቸው ከየትምህርት ተቋማቱ ተመርቀው የሚወጡ ምሉዕ እንዳልሆኑና ቀጣሪ አምራች ኢንዱስትሪዎችም እንደገና ሥልጠና ለመሥጠት የሚገደዱበት ሁኔታ ስለመኖሩም ይነገራል።

ዶክተር ዓለሙ ስለጉዳዩ ሲገልጹ «በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በንድፈ ሀሳብ የሚያገኙት እውቀት በተግባር እንዲደገፍ ዩኒቨርሲቲው በጋራ ከሚሠራቸው ተቋማት ጋር ባለው ስምምነት የተግባር ልምምድ እንዲያደርጉ ያመቻቻል። ከማዕድን ልማት ጋር የተያያዘውንም በተመሳሳይ ከተቋማት ጋር በመሥራት በዘርፉ የሚሰለጥኑ ተማሪዎች ሙሉ ሆነው እንዲወጡ ይደረጋል» ብለዋል።

እንደ ዶክተር ዓለሙ ገለጻ፤ ከተቋማት ጋር በትብብር በመሥራት በዘርፉ ብቃት ያለው ባለሙያ ለማፍራት በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ በኩል ከሚደረገው ጥረት በተጨማሪ፣ ዩኒቨርሲቲውም በተቻለ አቅሙ ተማሪዎች በተግባር የተደገፈ እውቀት እንዲያገኙ ጥረት ያደርጋል።

የዩኒቨርስቲው ቤተ-ሙከራ በተሻለ ሁኔታ የተደራጀና የተሟላ መሠረተ ልማት አለው። በቅርቡም ዩኒቨርሲቲው ከደቡብ ኮሪያ መንግሥት ባገኘው የገንዘብ ድጋፍ ዘመናዊ መሠረተ ልማት ለመሥራት በእንቅስቃሴ ላይ ይገኛል። «እነዚህ ሁሉ ጥረቶች ተስፋ ሰጪ በመሆናቸው ወደፊት ብዙ ችግሮችን መቅረፍ ይቻላል። እንዲህ ያሉ ጥረቶች ተጠናክረው ሲቀጥሉ ኢንዱስትሪዎች ብቃት ያለው የሰው ኃይል እንዲያገኙ ያስችላል» ብለዋል።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ዩኒቨርሲቲውም በዋናነት ተልዕኮ አድርጎ እየተንቀሳቀሰ ያለው የአምራች ኢንዱስትሪውን ዘርፍ ለማዘመንና፣ በዘርፉ ላይ የሚስተዋለውን ብቃት ያለው የሰው ኃይል እና የቴክኖሎጂ ክፍተት ለመሙላት ነው። ቅድሚያ ለኢንዱስትሪው ዘርፍ ቢሰጥም በግብርናው ዘርፍ ላይም ተዛማጅ የሆነ የቴክኖሎጂ ድጋፍ በማድረግ ያግዛል።

ከመግባቢያ ሰነድ የፊርማ ስምምነቱ መረዳት እንደሚቻለው፣ አምራች ኢንዱስትሪውን ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ አጋሮች ያስፈልጋሉ። የኢትዮጵያ ጂኦሎጂ ኢንስቲትዩት በኢትዮጵያ የማዕድን ሀብት የሚገኝበትን ሥፍራ በማመላከት፤ የኢንዱስትሪ ግብዓት አቅራቢ ኤጀንሲ አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚያስፈልጋቸውን ግብዓት በማቅረብ፤ የማዕድን ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ደግሞ ከግብዓት እስከ ምርት ያለውን ሂደት በመደገፍ በጋራ ይሠራሉ። አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ በበኩሉ በምርምር፣ በሥልጠና፣ በቴክኖሎጂ ሽግግርና በሌሎች መስኮች ድጋፍ ያደርጋል። እነዚህ አካላት በጋራ ለመሥራት የመግባቢያ ሰነድ የተፈራረሙ ሲሆን ማዕድን ሚኒስቴር ዋና ተልዕኮ አስፈጻሚ ሆኖ ይሠራል።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## የኢትዮጵያ መልኮች

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ኢትዮጵያ መልክ አላት..ገነትን እንደሚከቡ አራቱ ወንዞች ዘላለማዊ ቁንጅናን የታጠቁ። የኢትዮጵያ መልኮች እግዚአብሔራዊ መልኮች ናቸው..በመስጠት የከበሩ። ስይጥንናን የማያውቁ ብርሃናማ መልኮች። እንዲህ ስታስብ የአያቷ ድምጽ ከውጪ ተሰማት።

‹እግዚኦ..እግዚኦ..

‹ምነው እማማ ተዋቡ? ጋሽ ቢራራ ጠየቁ።

‹ዘይት ዘጠኝ መቶ ብር ገዝቼ መምጣቴ ነው። በዘመኔ እንዲህ ዓይነት የኑሮ ውድነት አላየሁም። ሰው በሰው ተጨካክኖ የለም እንዴ?

‹ስግብግቦች በዙ። ድሀ አስጨንቀው ኪሳቸውን ለማደለብ የሚሮጡ ነጋዴዎች በረከቱ። ምርት ጠፍቶ እኮ አይደለም በአቋራጭ ለመበልጸግ የሚፈልጉ አንዳንድ ስግብግብ ነጋዴዎች የፈጠሩት ነው። የባሰ እንዳይመጣ መጸለይ ነው›።

‹ከዚህ በላይ ምን የባሰ ሊመጣ በሉ? እኔ የማውቃት ኢትዮጵያ እንዲህ አልነበረችም። በነጣ እየሰጠን፣ እየተቀበልን ቀን የወጣን ነበርን። እግዚኦ ነው..እግዚኦ.. እግዚኦ።

‹ምርት የሚደብቁ ወንጀለኛ ነጋዴዎችን በመጠቆምና ለሕግ በማቅረብ ሕዝባችንን ከዚህ መከራ መታደግ አለብን። መንግሥት ብዙ ጥረት እያደረገ ነው እኛም እንደ ዜጋ እኚህን ሌቦች በማጋለጥ ከመንግሥት ጎን መቆም አለብን። እነሱ እስካሉ ድረስ ይሄ የኑሮ ውድነት እልባት አይኖረውም።

‹ሰው እንዴት በሰው እንዲህ ይጨክናል? ኢትዮጵያዊነት መልኩን ሲያጣ ያለዛሬ አላየሁም። የእኔ ኢትዮጵያ እንዲህ አልነበረችም..የልጆቼ ኢትዮጵያ እንዲህ መሆኗ ያሳዝናል። መስጠትን የመሰለ በረከት እኮ የለም። ድሀ አስጨንቆ የሚገኝ ትርፍ ርባና የለውም። ይዞ ነው የሚጠፋው። በሉ እስኪ ሰላም ይዋሉ..

እማማ ትዋቡ የገዙትን አምስት ሊትር ዘይት አራት ትናንሽ የሀይላንድ ፕላስቲክ ላይ ቀንሰው...›ነፃነት..አንቺ ነፃነት› ሲሉ ልጃቸውን ተጣሩ።

‹አቤት እማ? አለች ከውጪ ወደ ቤት እየገባች። እማ ነው የምትላቸው..እናትነትን ከአያትነት ጋር በአንድ ቀላቅለው የሰጧት እሳቸው ናቸው። እማ በዚህ ዓለም ያለ ድንቅ ስም ይመስላታል። ከዚህም በላይ ድንቅና ማራኪ ስም ቢኖር በዛ ትጠራቸው ነበር። ግን አላገኘችም። በአያትነት ውስጥ ከእናትነት የገዘፈ ሴትነት ያለ ይመስላታል። በሴትነት ውስጥ ዘመን የዋጀው ዕድሜ ጠገብ ሌላ ሴትነት ያለ ይመስላታል።

እማማ ተዋቡ ዘይት የነካ እጃቸውን ባደፈ ቀሚሳቸው እየጠረጉ ‹በይ አንዱን ለእትዬ በየነች፣ አንዱን ለጋሽ ፍሰሀ፣ የቀሩትን ደግሞ ለላቀችና ለእማሆይ ወይኗ ሰጥተሽ ነይ። እኔ ስካፈልና ሳካፍል ነው ያደኩት። ድሀ በችግር ተቆራምዶ ለብቻ የሚኖሩት ሕይወት በፈጣሪ ዘንድ ያስጠይቃል። ኢትዮጵያዊነት መልኩ ይሄ ነው...ካለ ላይ እየገመሱ ለሌለው መድረስ። በይ እንዳልኩሽ አደራዬን ፈጽመሽ ነይ›።

ነፃነት ዘይቱን በፌስታል አንጠልጥላ ትወጣለች።

ልጃቸው ወጥታም እማማ ተዋቡ ያወራሉ። ቤቱ ውስጥ ብቻቸውን ናቸው ግን ያወራሉ...ከራሳቸው ጋር፣ መልኳ ከጠፋው ኢትዮጵያ ጋር። ‹ሰው ሰው መሽተት አለብን። በኑሯችን፣ በተግባራችን ፈጣሪን ማስደሰት ሰውኛ ግዴታችን ነው። መልካችን የጠፋው፣ ኢትዮጵያዊነታችን ያደፈው ከሰውነት ስለሸሸን ነው። ሰው መሆን አለብን። ድሀን ማስጨነቅ እግዚአብሔርን ማስጨነቅ ነው። ልቦቻችንን ቸርነት፣ ነፍሶቻችንን ርህራሄ ማስተማር አለብን። ስለሌላው አእምሯችን በጎ ነገር እንዲያስብ ልናሰለጥነው ይገባል። እኔነት ኢትዮጵያዊ አይደለም። ፈጣሪ አምላክ ከነዛ ሁሉ ባለጸጋ መካከል ሳትሰስት ያላትን አንድ ሳንቲም የጣለችውን እመበለት ነው ሌማቷን በእንጀራ፣ ገንቦዋን በወይን፣ ቤቷን በበረከት የሞላው። እኛም እንድንባረክ ሰው መሆን አለብን...ሰው።

ነፃነት እናቷ እንዳዘዟት ለአራቱም ጎረቤቶቻቸው ዘይቱን አከፋፈለች። ይሄ ሲሆን ከነዛ ምንም ከሌላቸው ጎረቤቶቿ ብዙ ነገር አስተውላ ነበር። ሳቅ ስሜት ብቻ ይመስላት ነበር ግን ሳቅ ከስሜት ባለፈ ነፍስ እንዳለው ከነዛ ሰዎች አስተዋለች። ሳቅ በድሀ ሲሳቅና በባለጸጋ ሲሳቅ አንድ ዓይነት እንዳይደለ፣ የድሀ ነፍሶች የሚያደምጣቸው ቢያገኙ የሚናገሩት ብዙ የምንምነት ታሪክ እንዳላቸው ይሄን ሁሉ አስተዋለች። ሰው.. ሰው የሚሸተው መቼ ነው ለሚለው የምንጊዜም ጥያቄዋ መልስ አገኘች..ለሌላው መኖር ሲችል ሲል። ከእያንዳንዳቸው ድሀ ጎረቤቶቿ ያየችውና የሰማችው የደስታ ልዕልና ነገዋን በመስጠትና ለሌሎች በመኖር አሻግራ እንድታይ አስገደዳት። ለካ ሰው በሰው ይኖራል፣ ለካ ነፍስ በነፍስ ሀሴት ታደርጋለች። ለካ ሀገር ማለት መተቃቀፍ ነው።

በመስጠት የናኘ ደስ ካላት ነፍስ አብራክ ውስጥ የሚነፍስ እግዚአብሔራዊ ንፋስ ሴትነቷን ተዋሃዳት። ከባለጸጎች ልቃ በእግዚአብሔር እንደተወደደችው እንደዛች ድሀ እመበለት ከእያንዳንዳቸው ሳቅ ውስጥ እየነፈሰ ወደ አያቷ የሚበን የብኩርና ወጀብ ታያት። አያቷና እኚህ አራት ጎረቤቶቿ ዛሬ ላይ መልኳ የጠፋው ኢትዮጵያን መሰሏቻቸው። ብዙዎቻችን አምጠን ልንወልዳት የምንፈልጋት ኢትዮጵያ እኚህን ነፍሶች ናት። ኢትዮጵያ ማንን ትመስላለች ላላት የምትመልሰው መልስ አላት..አያቷንና እኚህን አራት ጎረቤቶቿን ስትል። መስጠት ሙላትን አይጠይቅም። መስጠት በጎ ህሊናን ብቻ ነው የሚሻው። አያቷ ኖሯት አይደለም የሰጠችው.. ኢትዮጵያዊነት ያስተማራት ተካፍሎ የመብላት ባህል እንጂ። እኛም ሁላችንም የኢትዮጵያን መልክ ለመመለስ የራሳችንን መልክ መመለስ አለብን። ዘመናዊነት መስሎን ካጣፋነው እኛነታችን መታረቅ አለብን። ስልጣኔ መስሎን ካሸሸነው ባህልና ሥርዓት መወዳጀት አለብን። አራዳነት መስሎን ከተውነው የራስ እውነት መቅረብ አለብን። ኋላ ቀርነት መስሎን ከሰወርነው በአንድ መዐድ የመቋደስ ጥበብ መቀመጥ አለብን።

ሁሉም ሰው ሌላ ነው። አንዱ በሩን ዘግቶ የድሀውን ጩኸት ችላ ብሎ ዘመናዊነትን ለማምጣት ይታትራል። ሌላው ከኢትዮጵያዊነት ሸሽቶና አፈንግጦ፣ ድሀ እያስራበና እያስጨነቀ በራስ ወዳድነት ኪሱን ለማደለብ ይሯሯጣል። የተቀረው ጊዜና አጋጣሚዎችን እየጠበቀ በሌሎች ሞት፣ በሌሎች ስቃይ ቤቱን ይሠራል። ለራሱ እያሰበ፣ ለራሱ የሚኖርም ሞልቷል። እንደ አያቷ ዓይነት ጥቂት ነፍሶች ደግሞ ከራሳቸውም ከፈጣሪም ሳይሸሹ በምንምነት ውስጥ ታሪክ ይሠራሉ። ኢትዮጵያዊነትን ታቅፈው ለዛኛው ትውልድ ይንገዳገዳሉ።

ከተማው፣ መንገዱ አስገረማት። አገሩ፣ መንደሩ ደነቃት። ሁሉም ከአያቷ እውነት ውጪ ነው። ሁሉም ለራሱ የሚኖር ነው። ኢትዮጵያ ጠፋችባት..። ይሄ ሁሉ ሰው እንደ አያቷ ደግ ልብ ቢኖረው ኖሮ ይሄ ሁሉ ችግረኛ፣ ይሄ ሁሉ ርሀብተኛ ባልኖረ ነበር ስትል አሰበች። በደግነትና በመልካምነት የአያቷን ነፍስ ተጋርታ በቀሪ ዘመኗ ሁሉ የጠፋችውን ኢትዮጵያ ፈልጋ ለማግኘት ለራሷ ቃል ገባች።

ነገ እንደ አያቷ ሴት ከመሆን ውጪ አማራጭ የላትም። ነገ እንደ አያቷ ከማሰብ ውጪ እውቀት አይኖራትም። ነገ እንደ አያቷ በመስጠት ከመሰልጠን ሌላ ስልጣኔ አይኖራትም። ነገ ላይ እውቀትና ጥበቧ ሁሉ ከአያቷ ሀበሻነት ውስጥ የሚቀዳ ይሆናል።

ኢትዮጵያ ናፈቀቻት። ኢትዮጵያን ፈልጋ የምታገኛት በአያቷ ነፍስ ላይ ነው። ወደ ቤቷ ገሰገሰች..

አያቷ ትምህርት ቤቷ ናት..የእውቀት፣ የጥበብ እልፍኟ። አያቷ የስልጣኔ ደብሯ ናት..ሀበሻዊነትን ያጠናችበት።

# ዓለም አቀፍ



## በሊቢያ ለኑክሌር ግንባታ የሚውል የዩራኒየም ንጥረ ነገር መጥፋቱን ተመድ አስታወቀ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ሊቢያ ውስጥ ከሚገኝ አንድ የማከማቻ ስፍራ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ኪሎ ግራም የሚመዝን የዩራኒየም ንጥረ ነገር መጥፋቱን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (የተመድ) የኑክሌር ተቆጣጣሪ አካል አስታወቀ።

ዓለም አቀፉ የአውቶሚክ ኃይል ኤጀንሲ (አይኤኢኤ) ሊቢያ ውስጥ በሚገኝ እና ስፍራውን በይፋ ባልጠቀሰው ቦታ ላይ ተቆጣጣሪዎቹ በዚህ ሳምንት መጀመሪያ ባደረጉት ጉብኝት ነው የንጥረ ነገሩ መጥፋት የታወቀው።

ተቆጣጣሪዎቹ በማከማቻው ስፍራው ከዚህ ቀደም የነበሩ ከሁለት ቶን በላይ የሚሆኑ የዩራኒየም ንጥረ ነገር የያዙ 10 በርሜሎች የደረሱበት አለመታወቁን ገልጿል።

ዩራኒየም ክምችቱ በአግባቡ እና በሚታወቅ አካል ደኅንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ካልተያዘ የጨረር አደጋ እና የኑክሌር ጦር መሣሪያ ስጋት ያስከትላል ማለቱን ቢቢሲ ዘግቧል።

የአውቶሚክ ኃይል ኤጀንሲው ባወጣው መግለጫ የጠፋው የዩራኒየም ንጥረ ነገር እንዴት ከነበረበት ስፍራ ሊወጣ እንደቻለ እና አሁን ያለበትን ቦታ በተመለከተ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት ምርመራ እንደሚያካሂድ አስታውቋል።

ለኑክሌር ግንባታ የሚውለው እና 2 ነጥብ 5 ቶን የሚመዝነው ዩራኒየም ከነበረበት ስፍራ መቼ እንደጠፋ የታወቀ ነገር የለም።

የዓለም አቀፉ የአውቶሚክ ኃይል ድርጅት ተቆጣጣሪዎች ቦታውን ባለፈው ዓመት ለመጎብኘት ፍላጎት የነበራቸው ቢሆንም፣ በተለያዩ የሊቢያ ሚሊሻዎች መካከል ውጊያ እየተካሄደ ስለነበረ ወደ ሌላ ጊዜ እንዲተላለፍ ተደርጓል።

ተቆጣጣሪው አካል እንዳለው የዩራኒየም ንጥረ ነገሩ ተከማችቶ የነበረበት ቦታ የሊቢያ መንግሥት ኃይሎች ከሚቆጣጠሩት አካባቢ ውጪ ነው።

ከአስር ዓመት በፊት የሊቢያው አምባገነን መሪ ኮሎኔል ሙአማር ጋዳፊ ከሥልጣን ከተወገዱ በኋላ፣ አገሪቱ በተፎካካሪ ፖለቲካዊ እና ወታደራዊ አንጃዎች መካከል ተከፋፍላለች።

በዚህም የሊቢያ ጊዜያዊ መንግሥት በዋና ከተማዋ ትሪፖሊ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን፣ ሌላኛው ኃይል ደግሞ ምሥራቃዊውን የአገሪቱን ክፍል ተቆጣጥሮ ይገኛል።

## የአሜሪካ ባለስልጣናት ቻይናዊው ባለሀብት 1 ቢሊዮን ዶላር አጭበርብሯል የሚል ክስ አቀረቡ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



ጉዎ ዌንጋይ

የአሜሪካ ባለስልጣናት ኑሮውን ኒውዮርክ ያደረገ አንድ ቻይናዊ ባለሀብት አንድ ቢሊዮን ዶላር አጭበርብሯል የሚል ክስ አቅርበዋል።

ጉዎ ዌንጋይ የተባለው ቻይናዊ በኢንተርኔት፣ ባንክና የደህንነት ሥርዓት በማጭበርበር እንዲሁም ሕገወጥ ገንዘብን ሕጋዊ ለማስመሰል በመሞከር ክስ ቀርቦበታል።

የቻይናን መንግሥት በመተቸት የሚታወቀው ጉዎ የቀድሞው የኋይት ሃውስ ዋና የስትራቴጂ ሰው ተባባሪም ነበር።

ባለሀብቱ ከታሰረ ከጥቂት ሰዓታት በኋላ በማንሃተን የሚገኘው አፓርታማው ላይ እሳት ተቀስቅሷል። የከተማው እሳት አደጋ መከላከል መስሪያ ቤቱ እሳቱ በቁጥጥር ስር እንደዋለና የደረሰ ጉዳት እንደሌለ ገልጾ የአደጋው መንስኤ እየተጣራ ነው ብለዋል።

ቀደም ብሎ ባለሀብቱ ጉዎ በማህበራዊ ሚዲያ ባሰራጨው መልዕክት እጁ ታስሮ ከአንድ ሰዓት በላይ ምርመራ እንደተደረገበት መግለጹን ቢቢሲ ዘግቧል።

ባለሀብቱ በተለያዩ ስሞች የሚጠራ ሲሆን ትናንት ረቡዕ በቀረበው የክስ መዝገብ ላይ ሆን ዋን ካውክ በሚል ስያሜ ተጠቅሷል።

ጉዎና አጋራቸው የመገናኛ ብዙኃን ቢዝነስ ላይ እናሳትፋ ችኋለን በሚል በማህበራዊ ሚዲያ አማካኝነት ከተጠቃሚዎች አንድ ቢሊዮን ዶላር ማሰባሰባቸውን የቀረበባቸው ክስ ያስረዳል።

በተጨማሪም ከተጠቃሚዎች ገንዘብ ለመስረቅ ክሪፕቶከረንሲ ተጠቅመዋል የሚል ክስ ቀርቦባቸዋል።

ባለጸጋው የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ ላይ ያለውን ተቃውሞና ከፍተኛ ስም ካላቸው የአሜሪካ ባለስልጣናት ጋር ያለውን ግንኙነት በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ተከታዮችን በማህበራዊ ሚዲያ እንዲያገኝ አስችሎታል። አብዛኞቹ ተከታዮች በምዕራባውያን አገራት የሚኖሩ ቻይናውያን ናቸው።

አቃብያነ ሕግ ግለሰቡ ማህበራዊ ሚዲያ ያለውን ስም ለንግድ ሥራ በሚል ገንዘብ ማሰባሰቢያ እንዳደረጉት ጠቅሰዋል። ሆኖም ያገኙትን ገንዘብ ወደንግድ ሥራ ከማዋል ይልቅ ከራሳቸው ጋር ወደ ተያያዘ የግል ገንዘብ ቋት ወስደውታል የሚል ክስ ቀርቦባቸዋል።

የተሰበሰበውን ገንዘብ 4 ሺህ 345 ካሬ መሬት ለሚሸፍን እና በኒውጀርሲ ለሚገኝ መሬት፣ እጅግ ቅንጡ መኪናዎችና ወደ 1 ሚሊዮን ዶላር የሚጠጋ ገንዘብ ለሚያወጡ የቻይናና ፐርዥያ ምንጣፍ ለመግዛት መዋሉ ተገልጿል።

አቃብያነ ሕጉ ከተሰበሰበው ገንዘብ 1 ሚሊዮን ዶላር ከፍተኛ ስጋት ለተጋረጠበት ንግድ መዋሉን ገልጸው የተቀረው ግን 140 ሺህ ዶላር ለሚያወጣ ፒያኖ፣ ለ62 ሺህ ዶላር ቴሌቪዥን፣ ለ53 ሺህ ዶላር የሳሎን እሳት ማያያዣ እና መሰል ቅንጡ ምርቶች ግዢ መዋሉን ጠቁመዋል።

ከባለፈው መስከረም ወር ጀምሮ የአሜሪካ መንግሥት ከ21 የተለያዩ ባንኮች ወደ 634 ሚሊዮን ዶላር የሚጠጋ ገንዘብ አግዷል።

ጉዎ ሁለት ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶችን አቋቁሜያለሁ በሚል የቻይና መንግሥትን የሚቃወሙ ተከታዮችን ለማፍራት መሞከሩም በክሱ ተመላክቷል።

ባለጸጋው በሪል እስቴት ግንባታ ላይ የተሰማራ ሲሆን እንደ አውሮፓውያኑ በ2014 አገሩን ለቆ ከመሄዱ በፊት በቻይና ከሚገኙ ባለሀብቶች አንዱ ነበር።

በ2017 በቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ ጫና ይደርስብኛል በሚል የአሜሪካ መንግሥትን ጥገኝነት ጠይቋል።

# ስፖርት





## ቀጣይ የፕሪሚየር ሊግ ጨዋታዎች አዳማና ሐዋሳ ይካሄዳሉ

**ቦጋለ አበበ**

በ2015 በቤትኪንግ የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ በ17ኛ ሳምንት መርሃግብር ሊካሄዱ የነበሩ ቀሪ ጨዋታዎች ለሌላ ተስተካካይ መርሃ ግብር መዘዋወራቸው ይታወቃል። በቤትኪንግ የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ 2015 በ17ኛ ሳምንት በድሬዳዋ ስታዲየም ቅዳሜ መጋቢት 02/2015 ዓ.ም የመጀመሪያ ጨዋታ በ10:00 ሰዓት ሃዋሳ ከተማ ከኢትዮጵያ ቡና ያገናኘ ሲሆን ጨዋታው ያለምንም ግብ በአቻ ውጤት ተጠናቋል።

በመርሃ ግብሩ መሠረት ቀጣይ የሳምንቱ ጨዋታዎችን ለማድረግ ግን በድሬዳዋ ከተማ በጣለው ያልተጠበቀ ዝናብ ሜዳው በመበላሸቱና በቀላሉ ሊያገግም ባለመቻሉ አወዳዳሪው አካል ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በማየት ቀሪ የከተማው የመጨረሻ ጨዋታዎች መሰረዛቸው ይታወሳል።

በዚህም መሠረት ውድድሩ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ጨዋታዎች ተቋርጦ በተመረጠ ቦታ መካሄዱ ሲቀጥል ከ18ኛው ሳምንት በኋላ ባለው ወቅት በተስተካካይ መርሃ ግብር የሚካሄዱ ይሆናል። ለዚህም የሊጉ የበላይ አካል በሦስት ከተሞች የሚገኙ ስታዲየሞችን ከቀናት በፊት ተመልክቷል።

የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ አክሲዮን ማኅበር ከ18ኛው ሳምንት ጀምሮ የሚደረጉ የሊጉ ጨዋታዎችን ማከናወኛ ስታዲየም ለመወሰን የሊግ ካምፓኒው የቦርድ ሰብሳቢ መቶ አለቃ ፍቃደ ማሞ እና ሥራ አስኪያጁ ክፍሌ ሰይፈ ወደ አዳማ አምርተው ከከተማው ከፍተኛ ኃላፊዎች ጋር ተወያይተው የዩኒቨርሲቲውን ሜዳ ተዟዙረው ተመልክተዋል።



አዳማና ሐዋሳ ቀጣይ የፕሪሚየር ሊግ ጨዋታዎችን ለማስተናገድ ተመርጠዋል፣

በሌላ በኩል የሊግ ካምፓኒው የውድድር እና ሥነ ሥርዓት ሰብሳቢው ዶክተር ወገኔ ዋልተንጉስ ወደ ሀዋሳ አምርተው በተመሳሳይ ከከተማው ኃላፊዎች ጋር በመሆን የዩኒቨርሲቲውን ሜዳ የተመለከቱ ሲሆን ከመጫወቻ ሜዳው ባለፈም የልምምድ እና የሆቴል አቅርቦት በበቂ ሁኔታ መዘጋጀቱን እና በስታዲየሙ ላይ ተጨማሪ መብራቶች ዙሪያውን መገጠሙን በመቃኘት ውይይት ማከናወናቸው ተጠቁሟል።

የሊግ ካምፓኒው የቦርድ አባል አቶ አሰፋ ሆሲሶ፣ አቶ መንግሥቱ ሳሳሞ እና አንበሴ መገርሳ ባህርዳር ከተማ አምርተው ምልከታ አድርገዋል። ልዑኩ የባህርዳር ዓለም አቀፍ ስታዲየም በግንባታ ላይ በመሆኑ የዩኒቨርሲቲውን ስታዲየም ቃኝቷል።

ሦስቱን ሜዳዎች የተመለከቱት የካምፓኒው አባላት ውይይቶችን ካደረጉ በኋላ በቀጣይ ውድድሮቹን የሚያስተናግዱ ሁለት ሜዳዎችን ትናንት ይፋ አድርገዋል። በዚህም መሠረት ከ18ኛው ሳምንት አንስቶ ያሉት የመጀመሪያዎቹ አምስት ጨዋታዎች (እስከ 22ኛው ሳምንት) በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ሜዳ ላይ እንዲከናወኑ ተወስኗል። ቀሪዎቹ ከ23ኛው እስከ 27ኛው ሳምንት መርሃግብር ያሉት ጨዋታዎች ደግሞ በሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ ሜዳ ላይ እንዲካሄዱ መወሰኑ ታውቋል። በዚህ ሂደት ውስጥ በሁለቱም ሜዳዎች በ17ኛው ሳምንት ያልተካሄዱት ጨዋታዎችም በየጣልቃው በተስተካካይ መርሃግብር ይካሄዳሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ከ28ኛው እስከ 30ኛው ያሉት የመጨረሻዎቹ ሳምንታት ጨዋታዎች የት ይካሄዳሉ? የሚለው ጉዳይ ግን አልታወቀም፡፡

ቤትኪንግ የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ 2015 እስከ 17ኛው ሳምንት የመጀመሪያ ጨዋታ ድረስ በድሬዳዋ ስታዲየም የተደረገ ሲሆን፣ የ17ኛው ሳምንት ቀሪ ጨዋታዎችና ከ18ኛ ሳምንት በኋላ ያሉ ጨዋታዎች ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ መልስ የሚደረግ ይሆናል። ቀሪ ዝርዝር ጉዳዮችንም የሊግ ካምፓኒው ወደ ፊት እንደሚገልፅ ጠቁሟል።


## Invitation to Bid
## Tender No. ECWC-T/NCB/PG/96/2015

1. The Ethiopian Construction Works Corporation invites sealed bids under National Competitive Bidding (NCB) from registered suppliers for the supply of Attendance Machine
2. Whereas a supplier wishes to participate for this bid but not yet registered in the suppliers' list may apply to the relevant authority for registration.
3. The bidding document may be purchased by interested suppliers from the office of Local Procurement Team against payment of non-refundable fee of Birr 400.00(birr Four hundred) upon presentation of trade license renewed for the fiscal year,
4. This invitation for bid is open to all interested bidders regardless of their nationality and the bid evaluation and award shall be determined in accordance with the provisions indicated in the bidding document. The bidding document is prepared in English language.
5. Interested bidders shall submit the following evidence;
   -Trading License renewed for 2015 EC; and
   -Tax Clearance Certificate indicating the bidder is allowable to participate in any public tender,
   -Vat Registration certificate and
   -Registration certificate as supplier from the mandated public body,
6. Bids must be delivered or deposited in the Tender Box available at the office of the Local Procurement Team before the closing date and time on, April 04/2023 at 02:30 P.M.
7. Bids will be opened on, April 04/2023 at 03:00 P.M. in the Ethiopian Construction Works Corporation, Procurement Department Conference Room in the presence of bidders and/or their representatives who choose to attend.
8. All bids must be accompanied by a bid security; the amount of the Bid Proposal security shall be 300,000.00 (Birr Three hundred thousand). The bid security should be either in the form of Certified Payment Order (CPO) and Bank Guarantee in the name of Ethiopian Construction Works Corporation. Bid bond in the form of insurance bond or in any other form shall not be accepted.
9. The Ethiopian Construction Works Corporation reserves its rights to reject any or all bids.
10. Bidders may get further information at the following address:

**Local Procurement Team**
**Telephone No. +251118 134527 /. +251118722958**
**Addis Ababa, Ethiopia**
**Telegram address ECWC/ኢኮስኮ**
**Gurd Sholla, Behind Athletics Federation Building Near Andnet International School.**

**Ethiopian Construction Works Corporation**



## የጨረታ ጥሪ ማስታወቂያ
### የጨረታ ማስታወቂያ ቁጥር ECWCT-NCB-SOG-108/2015

የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን ቃሊቲና በተለያዩ ፕሮጀክቶች የሚገኙ የተለያዩ ቁርጥራጭ ብረታብረቶች ባሉበት ቦታና ሁኔታ በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመሸጥ ይፈልጋል፡፡

1. ተጫራቾች የግብር ከፋይ ምዝገባ ሰርተፍኬት (Tin Number)፣ የዘመኑን ግብር የከፈሉበት መረጃ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይ መሆናቸውን ማረጋገጫ ሰርተፍኬት በማቅረብ የጨረታውን ሰነድ የማይመለስ ብር 300 /ሶስት መቶ ብር/ በመክፈል ዘወትር በሥራ ሰዓት ጉርድ ሾላ በሚገኘው ዋናው መ/ቤት አሮጌው ህንፃ ግዥ ክፍል በአካል በመቅረብ መግዛት ይችላሉ፡፡
2. የጨረታው አሸናፊ የሚወሰነው በጨረታ ሰነድ ውስጥ የተመለከቱትን መስፈርቶች አሟልቶ ከፍተኛ ዋጋ የሚያቀርበው ሲሆን የጨረታ ሰነዱ የተዘጋጀው በአማርኛ ቋንቋ ነው፡፡
3. ተጫራቾች ጨረታውን ለዚህ ተግባር በተዘጋጀው ሣጥን በግዥ መምሪያ-1 ቢሮ ገቢ የሚያደርጉበት የመጨረሻ ቀን መጋቢት 26 ቀን 2015 ዓ.ም እስከ ጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ድረስ ብቻ ነው::
4. ተጫራቾች ለእያንዳንዱ ሎት የሚጫረቱበትን የእያንዳንዱን ሎት ዋጋ አስር በመቶ /10%/ የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ በተረጋገጠ CPO ወይም በባንክ ዋስትና ከመጫረቻ ሰነዳቸው ጋር ማቅረብ ይኖርባቸዋል በኢንሹራንስ ቦንድ /በሌላ መልክ የሚቀርብ ማንኛውም ማስከበሪያ ተቀባይነት የለውም፡፡
5. ጨረታው ተጫራቾች ወይንም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት መጋቢት 26 ቀን 2015 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡30 ጉርድ ሾላ በሚገኘው የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን ዋናው መ/ቤት ቅጥር ግቢ የስብሰባ አዳራሽ ይከፈታል::
6. መ/ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
7. ለበለጠ መረጃ በሚከተለው አድራሻ መጠየቅ ይችላሉ፡፡

**አድራሻ፡- ጉርድ ሾላ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ህንፃ 200 ሜትር ገባ ብሎ**
**አንድነት ኢንተርናሽናል ት/ቤት ፊት-ለፊት በግዥ መምሪያ ቢሮ**
**ስልክ ቁጥር 0118-13 45 27 / 0118-72 29 58**
**አዲስ አበባ ኢትዮጵያ**

**የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን**